





# የአካባቢ ሳይንስ



## የተማሪ መጽሐፍ

## 3ኛ ክፍል

የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግሥት ትምህርት ቢሮ




# የአካባቢ ሳይንስ

## የተማሪ መጽሐፍ

## 3ኛ ክፍል


### አዘጋጆች፡-

1. ዳዊት አበበ(MSc.)
2. ይድነቃቸዉ አረጋ(MSc.)
3. ጌታቸዉ ኃይሌ(BSc.)

### አርታኢ፡-

1. አለሙ ወርቁ(MA)

### ጥራት አረጋጋጮች

1. ዘላለም ለገሰ(MSc.)
2. ዝናው ዱባለ(MSc.)
3. መሃመድናጂ እስማኤል(MA)

### ሰዓሊ፡-

1. ሃይማኖት ኬሜቶ

### ሌያውት ዲዛይን፡-

1. ኃይለማርያም መለሰ (MSc.)



የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግሥት ትምህርት ቢሮ

# © የቅጂ መብት

ይህ መጽሐፍ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅቶ በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት በኩል በተገኘ የገንዘብና የቴክኒክ ድጋፍ ተዘጋጅቶ አጠቃላይ የሕትመት ወጪው በደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ተሸፍኗል፡፡

የመጽሃፉ ሕጋዊ ቅጂ ባለቤት © 2015 ዓ.ም የደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ ነው፡፡

# ማውጫ


መግቢያ .......................................................................................i

## ምዕራፍ አንድ ........................................1

መገኛ.........................................................................................1

1.1. የዞናችን አንፃራዊ መገኛ.........................................................3

1.2. የዞናችን ፍፁማዊ መገኛ.........................................................5

1.3. በዞናችን ጠቃሚ ቦታዎች መገኛ ...............................................8

1.4. የአጐራባች ዞኖች ስፍራና ስሞች...............................................9

## ምዕራፍ ሁለት ...................................... 14

ሳይንስን ማስተዋወቅ...................................................................14

2.1. ምግብ እና ጤና .....................................................................15

2.2. የምግብ አስፈላጊነት..................................................................16

2.2.1. አራቱ ዋና ዋና የምግብ ክፍሎች ..............................................17

2.2.2. የምግብ ብክለት መንስኤዎች ...................................................20

2.3.የግል ንፅህና አጠባበቅ ..............................................................23

2.3.1. ንፅህናችንን ለምን እንጠብቃለን?..............................................24

2.3.2. የግል ንፅህና ጉድለት በሌሎች ሰዎች ላይ ምን ሊያስከትል ይችላል? .................25

2.3.3. በንጽህና ጉድለት ምክንያት የሚከሰቱ በሽታዎች ...............................26

2.3.4. ጤናማ እና የታመሙ ሰዎችን ማነፃፀር ........................................26

2.3.5. ለታመሙ ሰዎች ትኩረት እና እንክብካቤ መስጠት...............................27

2.4. የቁስ አካላዊ ለውጦች ...............................................................29

2.5. የብርሃን አስፈላጊነት...................................................................33

# ምዕራፍ ሦስት...................................... 37

## የተፈጥሮ አካባቢ ........................................................................37

3.1. የዞናችን የአየር ንብረት ......................................................................38

3.1.1. በአየር ሁኔታ እና በአየር ንብረት መካከል ያለው ልዩነት ................................39

3.1.2. የአየር ንብረት አካላት ......................................................................40

3.1.3. የአየር ንብረት ቁጥጥር ......................................................................41

3.2. የተፈጥሮ ሀብት ......................................................................43

3.2.1. የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ ሀብቶች ......................................................................44

3.2.2. በዞናችሁ ውስጥ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶች ......................................................................45

3.2.3. በዞናችሁ ውስጥ የእያንዳንዱ የተፈጥሮ ሀብቶች አጠቃቀም እና እሴቶች............50

3.3.በዞናችሁ ውስጥ ለመኖር እና ለልማት የተፈጥሮ ሀብቶች አስፈላጊነት ...................51

3.3.1.በዞናችሁ የተፈጥሮ ሀብት የመመናመን፣ የመበላሸት መንስኤዎች እና ውጤቶች.53

3.3.2.በዞናችሁ የሀገር በቀል እና መደበኛ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና የጥበቃ እርምጃዎች56

3.3.3.በዞናችሁ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና የጥበቃ ጥቅሞች......................................58

3.4. ተገቢና ተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ልምዶች ......................................................59

3.5. ተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ልምዶች እና ዉጤቶች......................................62

# ምዕራፍ አራት...................................... 66

## ማህበራዊ አካባቢ ........................................................................66

4.1. የባህል ብዝሃነት......................................................................67

4.1.1.ባህል እና ባህላዊ ልምዶች ትርጓሜ እና ምሳሌዎች ......................................68

4.1.2.የተለያዩ ባህሎች በዞናችሁ......................................................................69

4.1.3.በዞናችሁ የሚገኙ ቋንቋዎች......................................................................72

4.1.4.በዞናችሁ ለተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ አስፈላጊ ባህላዊ ልምዶች.................................73

4.1.5.በዞናችሁ ዋና ዋና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች......................................................73

4.1.6.የእኮኖሚ እንቅስቃሴ በተፈጥሮ ሀብት ላይ ያለዉ ተፅዕኖ ....................................76

4.1.7.የግብይት ትርጓሜ ......................................................................77

4.1.8. በዞናችሁ ለገበያ የሚቀርቡ የተፈጥሮ ሀብት እና ምርቶቻቸዉ ............................ 78
4.1.9. በዞናችሁ የተፈጥሮ ሀብት እና ምርቶቻቸዉ የግብይት ልምዶች.......................... 78
4.1.10. ለሰዎችና የሸቀጦች የመጓጓዣ መንገዶች ...................................................... 79

## ምዕራፍ አምስት ........................................ 83

የተለየ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ........................................................83

5.1. የመንገድ ደህንነት ........................................................................................ 84
5.2. ኤች አይ ቪ/ ኤድስ ......................................................................................... 89

# መግቢያ

የአካባቢ ሳይንስ ትምህርት በተማሪዎች አካባቢ የሚገኙ ማህበራዊና ተፈጥሮአዊ ገፅታዎችን በተሟላ ሁኔታ ለማወቅ፣የእርስ በርስ ግንኙነታቸዉን ለመረዳትና የእነዚህን ዕዉቀት ለሰዉ ልጅ ጥቅም ለማዋል የሚረዳ ትምህርት ነዉ፡፡ይህ ትምህርት የሕብረተሰብ ሣይንስ ፣የተፈጥሮ ሣይንስ፣ የአካባቢ ትምህርት እና የጤና ትምህርትን ዕዉቀት፣ ክህሎት፣ ልምድ፣ችሎታ፣ዝንባሌና አመለካከት በማዋሀድ ለመማር ምቹ በሆነ ሁኔታ የተቀናጀ ትምህርት ነዉ፡፡ በዚህ መሠረት የ3ኛ ክፍል የአካባቢ ሳይንስ የመማሪያ መጽሐፍ ለደረጃዉ የተዘጋጀዉን ሲለበስ መነሻ በማድረግ በአዱሱ መርሃ ትምህርት ላይ ተመስርቶ የአካባቢን ነባራዊ ሁኔታዎች በማገናዘብ የተዘጋጀ ሲሆን በውስጡ አምስት ምዕራፎችን አካቷል፡፡ እነዚህም መገኛ፣ ሳይንስን ማስተዋወቅ፤ ተፈጥሯዊ አካባቢያችን፣ማህበራዊ አካባቢ እና የተለየ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች የሚሉትን ይዘቶች በተቀናጀና ለመማር ማስተማር በሚያመች መልኩ እንዲያካትቱ ተደርጎ የተዘጋጀ ነዉ፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራትና ክንዋኔዎችን በሚገባ በመረዳትና በተናጠልም ሆነ በቡድን በመስራት የዕዉቀት አድማሳችሁን ለማስፋትና ከትምህርቱ ክህሎትና ዝንባሌ ለማዳበር የበኩላቸዉን ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

# ምዕራፍ አንድ

# መገኛ

## 1. የዞናችን መገኛ

### ከምዕራፉ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምራችሁ ስታጠናቅቁ:-

- አቅጣጫን የመለየት ክህሎትን ታዳብራላችሁ::
- ንድፎችን እና ካርታዎችን በመጠቀም ከሰዎች ጋር ለመግባባት ፈቃደኛነትን ታሳያላችሁ::
- በዞናችሁ አንጻራዊ ቦታን ትገልጻላችሁ::
- ፍፁማዊ መገኛ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ትገልጻላችሁ::
- የአካባቢያችሁን አንጻራዊ መገኛ ትለያላችሁ::
- የዞናችሁን ፍፁማዊ መገኛ ታመለክታላችሁ::
- ኬክሮስ እና ኬንትሮስ በመጠቀም በዞናችሁ ካርታ ላይ የቦታዎችን አቀማመጥ ታሳያላችሁ::
- በዞናችሁ ውስጥ ጠቃሚ ቦታዎችን ለማመልከት ኬክሮስ እና ኬንትሮስ ትጠቀማላችሁ::
- በዞናችሁ ውስጥ ጠቃሚ ቦታዎችን ለማመልከት የጎግል ካርታ(Google map) እና ጎግል የምድር መመልከቻ (Google earth) አጠቃቀም ዕውቀትን ታሳያላችሁ::

## በምዕራፉ የተካተቱ ይዘቶች

### የንዑስ ርዕሱ ይዘቶች

1.1. የዞናችን አንጻራዊ መገኛ
1.2. የዞናችን ፍፁማዊ መገኛ
1.3. በዞናችን ውስጥ ጠቃሚ ቦታዎች መገኛ
1.4. የአጎራባች ዞኖች መገኛ እና ስሞች

### መግቢያ

በሁለተኛ ክፍል የአካባቢ ሳይንስ ትምህርት የወረዳችሁን መገኛ፣ዋና ዋና የመሬት አቀማመጥ፣ፍፁማዊ እና አንጻራዊ መገኛ፣ጠቃሚ ቦታዎች፣ አጐራባች ወረዳዎች እና ስሞች የሚሉ ይዘቶችን ተምራችኋል፡፡በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ደግሞ የዞናችሁን መገኛ፣ፍፁማዊ እና አንጻራዊ መገኛ፣ ጠቃሚ ቦታዎችና አጐራባች ዞኖች መገኛ ስፍራ እና ስሞች የሚሉ ይዘቶች ተካተዋል፡፡



### መታወስ የሚገባቸው ቁልፍ ቃላት፡-

- ☑ አንጻራዊ መገኛ
- ☑ ኬክሮስ
- ☑ አጐራባች
- ☑ ፍፁማዊ መገኛ
- ☑ ኬንትሮስ
- ☑ ጠቃሚ ቦታዎች

## 1.የዞናችን መገኛ

### ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህን ንዑስ ርዕስ ተምራችሁ ስታጠናቅቁ፡-

- አራቱን መሰረታዊ አቅጣጫዎች የመለየት ችሎታን ታዳብራላችሁ፡፡
- ከአራቱ አቅጣጫዎች አንፃር በዞናችሁ ዉስጥ የሚገኙትን ጠቃሚ ቦታዎችን ታመለክታላችሁ፡፡
- የዞናችሁን አንፃራዊና ፍፁማዊ አቅጣጫን ትለያላችሁ፡፡
- ንድፎችን እና ካርታዎችን በመጠቀም ከሰዎች ጋር ለመግባባት ፍቃደኛነትን ታሳያላችሁ፡፡

ዞን ማለት ከወረዳ ቀጥሎ የሚገኝ መንግሥታዊ አስተዳደር እርከን የያዘ ሆኖ በውስጡ የተለያዩ ወረዳዎችን ያቀፈ ነው። እንዲሁም ዞን ልዩ ልዩ መልካዓምድራዊ ገጽታዎች፣ ማህበራዊ ተቋማት፣ ሀይማኖታዊ ተቋማት እና የተፈጥሮ ሃብቶችን ወዘተ... የያዘ ሰፊ መሬት ሆኖ በዉስጡ ህዝቦችን ያካተተ መንግሥታዊ የአስተዳደር መዋቅር ነው።

## የተግባር 1.1: የቡድን ዉይይት

**ዓላማ:-** የዞናችሁን መሰረታዊ አቅጣጫዎችን መለየት

**መመሪያ:-** በቡድን በመወያየት መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ

የመወያያ ጥያቄዎች:-

1. መሰረታዊ አቅጣጫዎችን ዘርዝሩ።
2. የምትኖሩበትን አካባቢ ወይም ዞን አቅጣጫ ከሌሎች ዞኖች /ልዩ ወረዳ/
3. እንዴት ለይታችሁ ማወቅ ትችላላችሁ?

የአንድን ቦታ መገኛ በአንፃራዊና በፍፁማዊ መንገድ ለይቶ መግለፅ ይቻላል። ስለዚህ የዞናችሁን መገኛ ለመግለፅ ሁለት መንገዶች ትጠቀማላችሁ።

**እነሱም:-**


1. አንፃራዊ መገኛ
2. ፍፁማዊ መገኛ ናቸዉ።

## 1.1. የዞናችን አንፃራዊ መገኛ

አንፃራዊ መገኛ አንድ ቦታ ከሌላ ቦታ አንፃር የሚገኝበትን አካባቢ ለማወቅ የምንጠቀምበት ዘዴ ነዉ። ለምሳሌ:- በስተግራ፣ በስተቀኝ፣ ከበስተኋላ፣ ከፊትለፊት፣ከታች ፣ከላይ በማለት መግለፅ ይቻላል።በተጨማሪም የአንድን ነገር አንጻራዊ መገኛ ከአንድ ቋሚ አካባቢ አንፃር ተነስተን በአራቱ መሰረታዊ አቅጣጫዎች ማመላከት ይቻላል።

የዞናችሁን አንፃራዊ መገኛ ለማወቅ በመጀመሪያ አራቱን አብይ አቅጣጫዎች ማወቅ ያስፈልጋል።እነዚህም ሰሜን፣ደቡብ፣ምስራቅ እና ምዕራብ ናቸው።

የምንገኝበት ዞን ከሌሎች ዞኖች ወይም ወረዳዎች ለይተን ለማወቅ በአንጻራዊ መገኛ ማመልከት ይቻላል፡፡




ሥዕል-1.1.አራቱ መሰረታዊ አቅጣጫዎች

የተግባር 1.2: **የቡድን** ውይይት

**ዓላማ:-** የዞናችሁን አንፃራዊ አቅጣጫና አዋሳኝ ዞን/ልዩ ወረዳ/ ወይም ክልል መለየት

**መመሪያ:** ከታች በቀረበው የደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል ካርታ/ሥዕል1.2/ ተጠቅማችሁ በቡድን በመወያየት መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ

1. እናንተ የምትገኙበት ዞን፡-


   በሰሜን ከ____________ዞን /ልዩ ወረዳ/ ወይም ክልል ይዋሰናል፡፡

   በደቡብ ከ____________ዞን /ልዩ ወረዳ ወይም ክልል ይዋሰናል፡፡

   በምስራቅ ከ____________ዞን /ልዩ ወረዳ/ ወይም ክልል ይዋሰናል፡፡

   በምዕራብ ከ____________ዞን /ልዩ ወረዳ/ ወይም ክልል ይዋሰናል፡፡

2. እናንተ የምትገኙበት ዞን /ልዩ ወረዳ/ የክልሉ ሰሜናዊ ክፍል፣ ደቡባዊ ክፍል፣ ምስራቃዊ ክፍል ወይም ምዕራባዊ ክፍል መሆኑን ለዩ፡፡




ሥዕል1.2.የደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል ንድፍ ካርታ

## 1.2. የዞናችን ፍፁማዊ መገኛ

ፍፁማዊ መገኛ አንድ ቦታ በካርታ ላይ ያለውን ትክክለኛ መገኛ የሚገልፅ ነዉ፡፡

ፍፁማዊ መገኛን ለመግለፅ እንደ ኬክሮስና ኬንትሮስ ያሉ መጋጠሚያዎችን /intersection point/ በመጠቀም ማወቅ ይቻላል፡፡


### ከዚህም አንፃር

1. ኬክሮስ ማለት አንድ ቦታ ከምድር ወገብ (መነሻ) በስተሰሜን ወይም በስተደቡብ ያለውን ርቀት በዲግሪ የሚገልፅ ነዉ፡፡እነዚህ መስመሮች ከምድር ወገብ ጋር ትይዩና በምድር ዙሪያ አግድም ይሠመራሉ፡፡

2. 2ኛ. የኬንትሮስ መስመር አንድ ቦታ ከጠቅላይ ሜሪዲያን (Prime meridian) በስተምዕራብ ወይም በስተምስራቅ ያለዉን ርቀት በዲግሪ የሚገልፅ ነዉ፡፡
3. የኬክሮስና ኬንትሮስ መስመሮች መለኪያዎች በዲግሪ (°)፣ በደቂቃ (') ወይም በሴኮንዶች (") ይገለጻሉ፡፡ከአንድ ትይዩ መስመር ወደ ሌላ ትይዩ መስመር ያለው አጠቃላይ ርቀት አሥራ አምስት ድግሪ (15°) ነዉ፡፡
4. ኬክሮስ በሚለካበት ጊዜ ከምድር ወገብ ዜሮዲግሪ (0°) ኬክሮስ ላይ እንደ መነሻ ያገለግላል፡፡እንዲሁም ዋናው ሜሪዲያን (prime meridian) ዜሮ ዲግሪ (0°) ኬንትሮስን የሚወክል የኬንትሮስ መለኪያ መነሻ ነጥብ ነው፡፡ እያንዳንዱ ኬክሮስ ወይም ኬንትሮስ የሚለካው በየትኛውም አቅጣጫ ከመነሻ ነጥብ ተነስቶ ነው፡፡

ኬክሮስና ኬንትሮስ መስመሮችን ተጠቅሞ የአንድን ቦታ ፍፁማዊ መገኛ ለማመልከት የሚረዱ ቅደም ተከተሎች

1. የሚፈለገዉን መገኛ ቦታ መለየት- ለምሳሌ፡-ከዚህ በታች ባለዉ ምስል ላይ ያለዉ ነጥብ "ሀ"ን መለየት፡፡
2. ከቦታዉ በመነሳት ከግርጌ የሚገኘዉን የኬክሮስ መስመር ድግሪ መዉሰድ፡፡ ከዚያም ከተነሳንበት ዲግሪ ወደ ላይ ያለዉን ልዩነት በድግሪ ማግኘትና በቀድሞዉ ድግሪ ላይ በመደመር የቦታዉን የኬክሮስ ድግሪ እናገኛለን፡፡
3. በመቀጠል ከቦታዉ ተነስተን በካርታዉ ላይ በስተምዕራብ የሚገኘዉን የቋሚ መስመር (ኬንትሮስ) ዲግሪ በመነሳት ከመነሻ ድግሪ ወደ ምስራቅ ያለዉን ልዩነት በመዉሰድ በቀድሞ ላይ ደምሮ ማስቀመጥ፡፡
4. ያገኘነዉን ዲግሪ ቀድመን ኬክሮስን እናስቀምጣለን በመቀጠልም የኬንትሮስ ድግሪዉን እንገልጻለን፡፡




ሥዕል1.3. የኬክሮስ እና ኬንትሮስ ምናባዊ መስመሮች

ቦታዉ የሚገኘዉ በ15⁰ ልዩነት የሚገኝ ቢሆን፡-

በዚሁ መሠረት ከኬክሮስ 45⁰ እንነሳና ቦታዉ አጋማሽ ላይ በመሆኑ የ15⁰ ድግሪ ግማሽ ማለትም 7.5⁰ እንደምርበታለን፡፡ ማለትም 45⁰+7.5⁰ = 52.5⁰ ኬክሮስ ሰሜን ሲሆን ኬንትሮሱ ደግሞ ከ30⁰ እንነሳና ቦታዉ አጋማሽ ላይ ያለ በመሆኑ በ30⁰ እና 45⁰ ልዩነት ማለትም የ15⁰ ግማሽ 7.5⁰ ልዩነት በ30⁰ ላይ እንደምራለን፡፡

ማለትም 30⁰ + 7.5⁰ = 37.5⁰ ኬንትሮስ ምስራቅ ይሆናል፡፡

በመሆኑም ቦታዉ ማለትም “ሀ” የሚገኝበት ፍፁማዊ መገኛ 52.5⁰ ኬክሮስ ሰሜንና 37.5⁰ ኬንትሮስ ምስራቅ ይሆናል ማለት ነዉ፡፡

በተጨማሪም የአንድን አካባቢ ፍፁማዊ መገኛን ለማግኘት በጎግል ካርታ እና ጎግል የመሬት መመልከቻ መጠቀም ይቻላል፡፡

ጎግል ካርታ

ጎግል ካርታ ማለት ከበይነ መረብ/ Internet/ ጋር የተያያዘ ሆኖ የመሬትን ሞዴል፣ቅርፅንና ርቀትን ማሳየት የሚችል ነገር ነዉ፡፡

### የጎግል ካርታ ጥቅም

1. ሰዎች የሚፈለጉትን ቦታ በቀላሉ በጥልቀት ለመለየት
2. የመሬትን ቅርፅ በቀላሉ ለመለየት

### የአጠቃቀም ዘዴ

1. የሚፈለገዉን ቦታ በቅድሚያ መለየት
2. ኬንትሮስና ኬክሮስን መለየት
3. ካርታዉን ከበይነ መረብ/ Internet/ በማዉረድ መመልከት

### የጎግል ካርታ ዓይነቶች

1. የመንገድ ጎግል ካርታ- መንገድ የሚያሳይ
2. የሳተላይት ጎግል ካርታ- ሳታላይትን በመጠቀም የተፈለገዉን ቦታ ለይቶ

### የሚያሳይ ካርታ

1. የመልካምድር ጎግል ካርታ- የመሬትን አቀማመጥና ቅርፅ የሚያሳይ ካርታ

**ተግባራዊ ክንውን 1.3**

ከላይ ባለው ሥዕል1.2 የደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል ንድፍ ካርታ ላይ መሰረት በማድረግ፡

1. የዞናችሁን መገኛ የኬክሮስና የኬንትሮስ መስመር በመጠቀም አሣዩ::
2. የዞናችሁን መገኛ ዘመናዊ ቴክኖሎጅዎችን በመጠቀም በጎግል ካርታ (Google map) እና ጎግል የምድር መመልከቻ (Google earth) በመጠቀም አሣዩ::

## 1.3. በዞናችን ጠቃሚ ቦታዎች መገኛ

በዞናችሁ ጠቃሚ ቦታዎች የሚባሉት ለህብረተሰብ ልማትና እድገት አስተዋፅኦ የሚያበረክቱ ታሪካዊና ተፈጥሮአዊ አካባቢዎች ናቸው::

**ለምሳሌ:-** የቅርሶች መገኛ ቦታዎች

በዚህም መሰረት በዞናችሁ ዉስጥ የሚገኙትን ጠቃሚ ቦታዎች በካርታ ላይ የኬክሮስና የኬንትሮስ መስመሮችን በማየት እንዲሁም ዘመናዊ ቴክኖሎጅዎችን

በመጠቀም በጉጎል ካርታ (Google map) እና ጉጎል የምድር መመልከቻ (Google earth) መለየትና ማወቅ ይቻላል።

### የተግባር 1.4: የቡድን ዉይይት

ከላይ ባለው ሥዕል 1.2 የደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል ንድፍ ካርታ ላይ መሰረት በማድረግ

1. በዞናችሁ ጠቃሚ የሆኑ ቦታዎች መገኛን የኬክሮስና የኬንትሮስ መስመር በመጠቀም አሳዩ።
2. በዞናችሁ ጠቃሚ የሆኑ ቦታዎች መገኛን ዘመናዊ ቴክኖሎጅዎችን በመጠቀም በጉጎል ካርታ (Google map) እና ጉጎል የምድር መመልከቻ (Google earth) በመጠቀም አሣዩ።

## 1.4. የአጎራባች ዞኖች ስፍራና ስሞች

### የተግባር 1.5: የቡድን ዉይይት

1. አጎራባች ማለት ምን ማለት ነዉ?
2. በሥዕል 1.2. የደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል ንድፍ ካርታ፣ እንዲሁም

ንጠረዥ1.1. እና1.2. ላይ መሰረት በማድረግ የዞናችሁን እና የአጎራባች ዞኖች ስምና አቅጣጫ ለዩ።

- አጎራባች ማለት በመሰረታዊ አቅጣጫዎች አንድን ቦታ/አካባቢ የሚያዋስኑ ቦታዎች ማለት ነው።

ሠንጠረዥ1.1. በደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል ዉስጥ የሚገኙ ዞኖች ከነዋና ከተማቸዉ

| ተ.ቁ. | የዞኑ መጠሪያ ስም | ዋና ከተማ |
|---|---|---|
| 1 | ጋሞ | አርባ ምንጭ |
| 2 | ጎፋ | ሳዉላ |
| 3 | ጌዲኦ | ዲላ |
| 4 | ጉራጌ | ወልቂጤ |
| 5 | ሀዲያ | ሆሳዕና |

| ተ.ቁ. | የዞኑ መጠሪያ ስም | ዋና ከተማ |
|---|---|---|
| 6 | ካምባታና ጠምባሮ | ዱራሜ |
| 7 | ስልጤ | ወራቤ |
| 8 | ደቡብ ኦሞ | ጂንካ |
| 9 | ወላይታ | ሶዶ |
| 10 | ሀላባ | ሀላባ ቁልቶ |
| 11 | ኮንሶ | ካራት |

ሠንጠረዥ1.2. በደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል ዉስጥ የሚገኙ ልዩ ወረዳዎች ከነዋና ከተማቸዉ

| ተ.ቁ | የልዩ ወረዳዉ መጠሪያ ስም | ዋና ከተማ |
|---|---|---|
| 1 | አማሮ | ኬሌ |
| 2 | አሌ | ገዋዳ |
| 3 | ባስኬቶ | ላስካ |
| 4 | ቡርጂ | ሶያማ |
| 5 | ደራሼ | ጊዶሌ |
| 6 | የም | ሳጃ |

## መልመጃ 1.1

**ሀ. የሚከተሉትን ዐረፍተነገሮች አንብባችሁ ትክክል ከሆነ እውነት ትክክል ካልሆነ ሀሰት በማለት መልሱ፡፡**

1. የአንድን አካባቢ ጠቃሚ ቦታ ለማወቅ ጎግል ካርታ መጠቀም ይቻላል፡፡
2. የአንጻራዊ መገኛ ለማወቅ ኬክሮስና ኬንትሮስ ብቸኛ አማራጮች ናቸዉ፡፡

**ለ.ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ሆሄ መርጣችሁ መልሱ፡፡**

1. ከሚከተሉት ዉስጥ የፀሐይ መግቢያ መሠረታዊ አቅጣጫ የቱ ነዉ?

   ሀ. ሰሜን ሐ.ደቡብ

   ለ. ምዕራብ መ. ምስራቅ

2. የኬንትሮስ መነሻ የሆነዉ የቱ ነዉ?

   ሀ. የምድር ወገብ ሐ. የካንሰር መስመር

   ለ. ጠቅላይ ሜሪዲያን መ. መልስ የለም

## ሐ.ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ስጡ።

1. የዞናችሁን አንፃራዊ መገኛ ለማወቅ የምትጠቀሙበት ማሳያ ምንድን ነዉ?
2. አጎራባች ማለት ምን ማለት ነዉ?

## ማጠቃለያ

- ዞን ከወረዳ ቀጥሎ የሚገኝ አስተዳደራዊ እርከን ነው።
- የዞናችን መገኛ ለመግለጽ አንጻራዊ መገኛ እና ፍፁማዊ መገኛ መንገዶችን እንጠቀማለን።
- አንጻራዊ መገኛ የምንኖርበትን አካባቢ መገኛ ከሌሎች ቦታ አንፃር ለማሳየት ይጠቅማል።
- ፍፁማዊ መገኛ የሚያመለክተው በካርታ ላይ የኬክሮስና ኬንትሮስ መስመሮች መጋጠሚያ በመጠቀም ነው።
- ኬክሮስ ከምድር ወገብ በስተሰሜን ወይም በስተደቡብ ያለውን የርቀት መለኪያ ነው።
- ኬንትሮስ ከዋናው ሜሪዲያን (Prime meridian) በስተምስራቅ ወይም በስተምዕራብ ያለውን የርቀት መለኪያ ነው።
- ኬክሮስና ኬንትሮስ በዲግሪዎች፣ በደቂቃዎች እና በሴኮንዶች የሚገለፁ ናቸው።
- በዞናችሁ ዉስጥ የሚገኙትን ጠቃሚ ቦታዎች በካርታ ላይ የኬክሮስና የኬንትሮስ መስመሮችን በማየት እንዲሁም ዘመናዊ ቴክኖሎጅዎችን በመጠቀም በጉጎል ካርታ (Google map) እና ጉጎል የምድር መመልከቻ (Google earth) መለየትና ማወቅ ይቻላል።
- ጠቃሚ ቦታ ማለት ለህብረተሰቡ ጥቅም የሚሰጥ የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ ሀብትን የያዘ ቦታ ነው።
- አጐራባች ማለት በመሰረታዊ አቅጣጫዎች አንድን ቦታ/አካባቢ የሚያዋስኑ ቦታዎች ማለት ነው።

## የምዕራፉ ማጠቃለያ የክለሳ ጥያቄዎች

**ሀ.የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች ካነበባችሁ በኋላ ትክክል ከሆነ “እውነት”ትክክል ካልሆነ ደግሞ “ሀሰት” በማለት መልስ/ሽ/፡፡**

1. ዞን ማለት ከቀበሌ ቀጥሎ የሚገኝ መንግሥታዊ አስተዳደር እርከን ነው፡፡
2. አንፃራዊ መገኛ የሚያመለክተው በምድር ገጽ ላይ ያለውን ቋሚ ቦታ ነው፡፡
3. ኬክሮስ ከምድር ወገብ በስተምስራቅ ወይም በስተምዕራብ ያለው የርቀት መለኪያ ነው፡፡
4. የኬንትሮስ መስመሮች ከጠቅላይ ሜሪዲያን ሰሜን ወይም ደቡብ ያለውን ቦታ በምድር ላይ ለመለካት ያገለግላሉ፡፡
5. የኬክሮስ መስመሮች ከምድር ወገብ ጋር ትይዩ ናቸው፡፡

**ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ሆሄ በመምረጥ መልስ/ሽ/፡፡**

1. የኬክሮስ እና የኬንትሮስ መለኪያ የሆነው የቱ ነው?
   ሀ. ሴኮንድ    ሐ. ደቂቃ
   ለ. ዲግሪ    መ. ሁሉም
2. ከአበይት አቅጣጫዎች ውስጥ የፀሐይ መዉጫን የሚያመለክት የቱ ነው?
   ሀ. ሰሜን    ሐ. ደቡብ
   ለ. ምስራቅ    መ. ምዕራብ
3. በዜሮ(0°) ኬንትሮስ ላይ የሚገኘው አብይ መስመር የቱ ነው?
   ሀ. የምድር ወገብ    ሐ. የካፕሪኮርን መስመር
   ለ. ጠቅላይ ሜሪዲያን    መ. የካንሰር መስመር
4. ዞን ከወረዳ አንጻር ሲታይ በመጠን____________
   ሀ. ያንሣል    ሐ. እኩል ነው
   ለ. ይበልጣል    መ. መልስ የለም

## ሐ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጫጭር መልሶችን ስጡ፡፡

1. አራቱን አበይት አቅጣጫዎችን ዘርዝሩ፡፡
2. አንፃራዊ መገኛ ማለት ምን ማለት ነው?
3. በምድር ዙሪያ ከደቡብ ንፍቀ ክበብ ወደ ሰሜን ንፍቀ ክበብ የተሰመሩ ምናባዊ መስመሮች ምን ይባላሉ?
4. ለዞናችሁ አጐራባች የሆኑ ዞኖችን ጥቀሱ፡፡
5. የአንፃራዊ መገኛና የፍፁማዊ መገኛ ልዩነቶችን ግለፁ፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ሳይንስን ማስተዋወቅ

## 2. ምግብና የቤተሰብ ደህንነት

ከምዕራፉ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች:-

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምራችሁ ስታጠናቅቁ:-

- ጤናማ ምግብ እና መጠጥ ለይታችሁ ትጠቀማላችሁ።
- ምግብን በአራት መሠረታዊ ቡድኖች ትመድባላችሁ።
- የምግብ ብክለትን ለመከላከል የሚረዱ ዘዴዎችን ትለያላችሁ።
- የጠጣር፣ፈሳሽ እና ጋዞችን ባህሪያትን ትገልጻላችሁ።
- የንጽህና አያያዝ ዘዴዎችን ትገልጻላችሁ።
- በነገሮች ሁኔታ ላይ የተደረጉ ለውጦችን ትገልጻላችሁ።
- የሁነት ለዉጦችን ለማሳየት ቀላል ሙከራዎችን ታካሂዳላችሁ።
- የተለያዩ የብርሃን ተግባራትን ትዘረዝራላችሁ።

### በምዕራፉ የተካተቱ ይዘቶች

2.1. ምግብ እና ጤና
2.2. የምግብ አስፈላጊነት
2.3. የግል ንፅህና አጠባበቅ
2.4. የቁስ አካላዊ ለውጦች
2.5. የብርሃን አስፈላጊነት

## መግቢያ

የሰዉ ልጅ በጤንነት ለመኖር እና የዕለት ተዕለት ሥራዉን ለማከናወን ምግብን በሚፈለገዉ ዓይነትና መጠን ማግኘት ተገቢ ነዉ።የተመጣጠነ የምግብ አመጋገብ ሥርዓትን የተከተለ ሰው ጤናማ ሆኖ ማንኛውንም ተግባር ለማከናወን ብቃት ይኖረዋል።በዚህ ምዕራፍ ዉስጥ ምግብ እና ጤና፣የምግብ አስፈላጊነት፣ የግል ንፅህና አጠባበቅ፣ የቁስ አካላዊ ለውጦች፣እንዲሁም የብርሃን አስፈላጊነት የሚሉት ይዘቶች ተካተዋል።በእነዚህ ዋና ዋና ርዕሶች ሥር የተዳሰሱ ሀሳቦች ከዕለት ተዕለት ኑሮአችን ጋር የተያያዙ ማለትም የምግብ አስፈላጊነት፤አራቱ መሠረታዊ የምግብ ቡድኖች፤ የምግብ ብክለት እና መንስኤዎች እና የግል ንፅህና አጠባበቅ ወዘተ...የሚመለከቱ የትምህርት ይዘቶች በዝርዝር ተካተዋል።

## 2.1. ምግብ እና ጤና

### መታወስ የሚገባቸዉ ቁልፍ ቃላት

- ☑ ምግብ
- ☑ የምግብ ክፍል
- ☑ የንፅህና ጉድለት
- ☑ የአመጋገብ ስርዓት
- ☑ የምግብ ብክለት

### ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህን ንዑስ ርዕስ ተምራችሁ ስታጠናቅቁ:-

- የምግብን አስፈላጊነት ትገልጻላችሁ።
- የተመጣጠነ ምግብ ጥቅምን ትገልፃላችሁ።

### የማነቃቂያ ጥያቄ

ምግብ ምንድን ነው?

ምግብ የሚበላ ወይም የሚጠጣና ለሰዉነታችን ጤንነትና ዕድገት ሊሰጥ የሚችል ንጥረ ነገር ነዉ። ምግብ ለሰዉ ልጅ ከሚያስፈልጉ መሠረታዊ ፍላጎቶቻችን መካከል አንዱ ነዉ።ሰውና ሌሎች ህይወት ያላቸው ነገሮች ያለምግብ መኖር አይችሉም።ምግብ ሃይልና ሙቀት በመስጠት፣ ሰውነትን

ከበሽታ ለመከላከል እና ለመገንባት ያገለግላል።ምግብን ከእፅዋትና ከእንስሳት እናገኛለን። ጤንነት ማለት ዉስጣዊ እና ዉጫዊ የአካል ደህንነት ማለት ሲሆን ጤንነታችንን ለመጠበቅ ደግሞ የተለያዩ የምግብ አይቶችን መመገብ ያስፈልጋል። አንድ ሰዉ የተሟላ ጤንነት እንዲኖረዉ በየዕለቱ የተለያዩ የምግብ ዓይነቶችን ወይም የተመጣጠነ ምግብ መመገብ አለበት።

የተመጣጠነ ምግብ የማይመገብ ሰው ደካማና በቀላሉ ለበሽታ የተጋለጠ ይሆናል።አዘውትራችሁ የተመጣጠነ ምግብ ከተመገባችሁ ጤናማ፣ ጠንካራ፣ ንቁና ጎበዝ ተማሪ ትሆናላችሁ።

## 2.2. የምግብ አስፈላጊነት

### ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

**ተማሪዎች ይህን ንዑስ ርዕስ ተምራችሁ ስታጠናቅቁ፡-**

- አራቱን የምግብ ክፍሎችን ትዘረዝራላችሁ።
- አራቱን የምግብ ክፍሎችን ጥቅም ትናገራላችሁ።
- የምግብ ብክለት መንስኤዎችን ትገልፃላችሁ።
- የምግብ መበከል የሚያስከትላቸዉን ጉዳቶች ትዘረዝራላችሁ።
- የምግብ ብክለት መከላከያ ዘዴዎችን ትለያላችሁ።

ጤናማ እንድንሆን፣ በቂ ኃይልና ሙቀት እንድናገኝና የተስተካከለ ዕድገት እንዲኖረን የተመጣጠነ የአመጋገብ ሥርዓት መከተል አለብን።በሀገራችን ብዙ ዓይነት ምግቦች ይገኛሉ።እነዚህ ምግቦች ከአንድ በላይ ንጥረ ምግቦችን ሊይዙ ይችላሉ።ነገር ግን ሁሉንም አስፈላጊ ንጥረ ምግቦች አጣምሮ በበቂ መጠን የያዘ ምግብ የለም።ስለዚህ የተለያዩ ምግቦችን በመመገብ የተመጣጠነ ምግብ ማግኘት ያስፈልጋል።

**የተመጣጠነ ምግብ መመገብ ለምን ይጠቅማል?**

የተመጣጠነ ምግብ መመገብ የሚከተሉትን ጥቅሞች ይሰጠናል።

- ሰውነታችንን ለመገንባትና የተጎዳ አካልን ለመጠገን
- በቂ ሀይልና ሙቀት ለማግኘት
- ሰውነታችንን ከበሽታ ለመካላከል

♣ የተስተካከለ፣ብርታት፣ጥንካሬ፣ ዕድገት እንዲኖረን ይረዳል።

## 2.2.1. አራቱ ዋና ዋና የምግብ ክፍሎች

### የተግባር 2.1: የቡድን ዉይይት


**ዓላማ:** አራቱን መሠረታዊ የምግብ ክፍሎችን መለየት

**መመሪያ:** በቡድን በመወያየት መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ

**የመወያያ ጥያቄዎች:**

1. ምግቦች ከመገኛ ምንጫቸዉና ከዓይነታቸዉ አኳያ በስንት ይመደባሉ? ዘርዝሯቸዉ።
2. በአካባቢያችሁ የምታዉቋቸዉን የምግብ ዓይነቶች በአራቱ መሰረታዊ የምግብ ክፍሎች መድቡ።


የምግብ አይነቶች እንደጥቅማቸውና እንደመገኛ ምንጫቸው ይመደባሉ። የመገኛ ምንጫቸውን መሰረት በማድረግ ቀጥሎ የተመለከቱት አራት መሰረታዊ የምግብ ክፍሎች አሉ።




ሥዕል 2.1.አራቱ የምግብ ክፍሎች

## 1. የአትክልትና ፍራፍሬ ክፍል


የአትክልትና ፍራፍሬ ምግቦች ሰውነታችንን ከበሽታ በሚከላከሉ ቪታሚኖችና ማዕድናት የበለፀጉ የምግብ ክፍሎች ናቸው፡፡እንደ ካሮት፣ ቀይሥር፣ ጎመን፣ ሰላጣ፣ ቆስጣ፣ ቃሪያና ቲማቲም አትክልት ሲሆኑ እንደ ብርቱኳን፣ ሎሚ፣ ሙዝ፣ መንደሪንና የመሳሰሉት ደግሞ የፍራፍሬ ምግቦች ናቸው፡፡




ሥዕል 2.2.የአትክልትና ፍራፍሬ ምግቦች

## 2. የእህልና ጥራጥሬ ክፍል

ይህ የምግብ ክፍል ለሰውነታችን ኃይልና ሙቀት ሰጭ ምግቦችን እንዲሁም ሰውነትን የሚገነቡና የሚጠግኑ ምግቦችን ያካተተ ነው፡፡ዳቦ፣ እንጀራ፣ ቂጣ፣ ገንፎ፣ ስንዴ፣ ባቄላ፣ ገብስ፣ በቆሎ፣ አደንጓሬ ፣ አተርና ምስር የእህልና ጥራጥሬ ምግቦች ናቸው፡፡




ሥዕል2.3. የእህልና ጥራጥሬ ምግቦች

## 3. የሥጋ ክፍል

በሥጋ ክፍል የሚመደቡ ምግቦች ሰውነትን በሚገነቡ በፕሮቲን ንጥረ ነገሮች የበለፀጉ ናቸው፡፡የበሬ ሥጋ፣ የበግ ሥጋ፣ የፍየል ሥጋ፣ የዶሮ ሥጋ፣ የአሣ ሥጋ እንዲሁም የአሳማ ሥጋ በዚህ የምግብ ክፍል ውስጥ ይመደባሉ፡፡




ሥዕል 2.4 የሥጋ ክፍል ምግቦች

## 4. የወተት ክፍል

የወተት ክፍል ለሰውነታችን በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ወተትና የወተት ተዋፅኦ ምግቦች በፕሮቲን የበለፀጉ በመሆናቸው ለአካል እድገትና ግንባታ እንዲሁም ለአጥንቶቻችንና ለጥርሶቻችን ጥንካሬ ጠቃሚ ናቸው፡፡ ወተት፣ እርጎ፣ አይብ፣ አሬራና አጓት የወተት ክፍል ምግቦች ናቸው፡፡




ሥዕል 2.5 ወተትና የወተት ተዋፅኦ

## መልመጃ 2.1

**ሀ. የሚከተሉትን ዐረፍ ተነገሮች ካነበባችሁ በኋላ ትክክል ከሆነ “እውነት”ትክክል ካልሆነ ደግሞ “ሀሰት” በማለት መልስ ስጡ፡፡**

1. ምስር የእህልና የጥራጥሬ ምግቦች ክፍል ዉስጥ ይመደባል፡፡
2. ምግብ ለሰዉ ልጅ ከሚያስፈልጉ መሰረታዊ ነገሮች አንዱ ነዉ፡፡

**ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ሆሄ በመምረጥ መልስ/ሽ/፡፡**

1. ከሚከተሉት ዉስጥ ከአትክልትና ፍራፍሬ ክፍል ዉስጥ የማይመደበዉ የቱ ነዉ?

   ሀ. አደንጓሬ ሐ. ሙዝ

   ለ. ሎሚ መ. መንደሪን

2. በቆሎ፣ስንዴና ጤፍ የሚመደቡት በ__________የምግብ ክፍል ነዉ፡፡

   ሀ.ሥጋ ሐ.የእህልና ጥራጥሬ

   ለ.አትክልትና ፍራፍሬ መ.ወተት

3. ከሚከተሉት ዉስጥ የእህልና ጥራጥሬ ምግብ ክፍል ዉስጥ የሚመደበዉ የቱ ነዉ?

   ሀ. ካሮት ሐ. ስንዴ

   ለ. ሰላጣ መ. ቃሪያ

### 2.2.2. የምግብ ብክለት መንስኤዎች

**የተግባር 2.2: የቡድን ዉይይት**

**ዓላማ፡-** የምግብ ብክለትና መንስኤዎችን መለየት

**መመሪያ፡-** በቡድን በመወያየት መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ

**የመወያያ ጥያቄዎች፡-**

1. የምግብ መበከል ማለት ምን ማለት ነው?
2. የምግብ መበከል ምክንያቶች ምንድን ናቸው?
3. የምግብ ብክለት መከላከያ ዘዴዎችን ዘርዝሩ፡፡

የምግብ መበከል ማለት ምግብ ለሰውነታችን የሚሰጠውን ጥቅም በተለያዩ ባዕድ ነገሮች ምክንያት መስጠት ሲያቋርጥና ለሰውነታችን ጎጂ ሲሆን ነው፡፡ምግብ የሚበከለው በተለያዩ ምክንያቶች ነው ፡፡ በዚህ መሰረት የምግብ መበከል ማለት በዓይን በማይታዩ በሽታን የሚያስከትሉ ጥቃቅን ህይወት ባላቸው ነገሮች/ጀርሞች/ መመረዝ ማለት ነው፡፡ብዙ ምግቦች በቀላሉ ይበከላሉ፡፡በጀርሞች የተበከሉ/የተበላሹ/ ምግቦች ተመጋቢውን ይመርዛሉ፤ለህመምም ያጋልጣሉ፡፡ ብሎም ለሞት ሊዳርጉ ይችላሉ፡፡

## የምግብ መበከልን የሚያስከትሉ ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

- ምግብ የሚያዘጋጀዉ ሰው የግል ንፅህና ጉድለት
- የምግብ መሥሪያ ዕቃዎች ንፅህና ጉድለት
- ምግብ የሚያዘጋጀዉ ሰው በተላላፊ በሽታ መጠቃት
- ለምግብ ዝግጅት የምንጠቀምበት ውሃ ንፅህና ጉድለት
- ሳይከደን የተቀመጠ ምግብ በአቧራ፣ በዝንብ፣ በአይጥ እና በተለያዩ በሽታ አምጭ ተዋስያን ንኪኪ ሲኖረዉ
- በመርዛማ ኬሚካሎች ምግቡ ሲበከል በምግብ ብክለት ምክንያት ለሚከሰት በሽታዎች ልንጋለጥ እንችላለን፡፡

በምግብ እና ዉሃ ብክለት እንደ ጃርዲያ፣ አሜባና ብልሃርዚያ በመሳሰሉት የአንጀት ጥገኛ ትላትሎች እንዲሁም እንደ ታይፎይድና ታይፈስ ባሉ በሽታዎች ልንጠቃ እንችላለን፡፡በዚህም ለከፍተኛ ትውከት፣ ተቅማጥ እና ከባድ ህመም እንጋለጣለን፡፡

## የማነቃቂያ ጥያቄ

ተማሪዎች! የምግብ ብልሽትን ለመከላከል የሚያስችሉ ዘዴዎች ምን ምን እንደሆኑ ለመምህራችሁ ግለፁ፡፡

## የምግብ ብክለት መከላከያ ዘዴዎች፡-

- የምግብ ማዘጋጃ ዕቃዎችን በሞቀ ውሃና ሣሙና በሚገባ ማጠብ ለምሳሌ:ድስት፣ መክተፊያ፣ ቢላዋና የመሳሰሉት
- ምግብ ሲዘጋጅ የእጆቻችንን ንፅህና መጠበቅ
- የምግብ ማቅረቢያና መመገቢያ ቁሳቁሶች እንደ ሰሀን፣ ጭልፋ፣ ማንኪያ

የመሳሰሉት ዕቃዎችን በንፁህ ውሃ ማጠብ

- በጥሬነታቸው የምንመገባቸው አትክልትና ፍራፍሬዎች እንደቲማቲም፣ ሰላጣና ብርቱካን የመሳሰሉትን ምግቦች ከመመገባችን በፊት በንፁህ ውሃ ማጠብ
- ለምግብ ዝግጅት የሚረዳ ንፁህ ውሃን መጠቀም
- በሽታ አስተላላፊ የሆኑ ዝንቦች፣ ትንኞች፣ በረሮዎች እንዲሁም አይጦች በምግብ ላይና በመመገቢያ ዕቃዎች ላይ እንዳያርፉ ሽፍኖ ማስቀመጥ
- ምግብን በበቂ ሁኔታ በማብሰል ጎጂ የሆኑ በሽታ አምጪ ጀርሞችን ማጥፋት
- የምግብ ማቆያ ዘዴዎችን በአግባቡ መጠቀም፡፡ለምሳሌ፡- ማቀዝቀዣ መጠቀም

## መልመጃ 2.2

**ሀ.የሚከተሉትንዐረፍተነገሮችካነበባችሁበኋላትክክልከሆነ“እውነት”ትክክል ካልሆነ ደግሞ “ሀሰት” በማለት መልሱ፡፡**

1. ለምግብ ዝግጅት የምንጠቀምበት ውሃ ንፅህና ጉድለት ካለበት የምግብ ብክለትን ሊያመጣ ይችላል፡፡
2. ምግብ ስናዘጋጅ የእጆቻችንን ንፅህና መጠበቅ ያስፈልጋል፡፡

**ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ሆሄ በመምረጥ መልስ/ሽ/፡፡**

1. የምግብ መበከል /ብልሽት/ ምክንያት የሆነዉ የቱ ነዉ?

    ሀ. ምግብን በበቂ ሁኔታ ያለማብሰል

    ለ. የምግብ ዝግጅት ዕቃዎች ንፅህና ጉድለት

    ሐ. የግል ንፅህና ጉድለት

    መ. ሁሉም መልስ ናቸዉ

2. የተበላሹ/የተበከሉ/ ምግቦች

    ሀ.ጣዕማቸዉን ይቀየራሉ

    ለ.በሽታ ያስከትላሉ

    ሐ.መጥፎ ሽታ ያመጣሉ

    መ. ሁሉም መልስ ናቸዉ

## 2.3. የግል ንፅህና አጠባበቅ



### መታወስ የሚገባቸው ቁልፍ ቃላት:-

- ☑ ጤናማ
- ☑ ተላላፊ በሽታ
- ☑ የግል ንፅህና

### ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህን ንዑስ ርዕስ ተምራችሁ ስታጠናቅቁ:-

- ስለ ግል ንፅህና አጠባበቅ ጠቀሜታ ትገልፃላችሁ::
- የግል ንፅህና አጠባበቅ ዘዴዎችን ትዘረዝራላችሁ::
- በግል ንፅህና ጉድለት የሚመጡ በሽታዎችን ትናገራላችሁ::
- ጤናማ እና የታመሙ ሰዎችን ባህሪያት ታነፃፅራላችሁ::
- ለታመሙ ሰዎች ትኩረትና እንክብካቤ ትሰጣላችሁ::

### የንዑስ ርዕሱ ይዘቶች

2.3.1. ንፅህናችንን ለምን እንጠብቃለን?

2.3.2. የግል ንፅህና ጉድለት በሌሎች ሰዎች ላይ ምን ሊያስከትል ይችላል?

2.3.4. በንጽህና ጉድለት ምክንያት የሚከሰቱ በሽታዎች

2.3.5. ጤናማ እና የታመሙ ሰዎችን ማነፃፀር

2.3.6. ለታመሙ ሰዎች ትኩረት እና እንክብካቤ መስጠት

### የግል ንፅህና አጠባበቅ

### የተግባር 2.3: የቡድን ዉይይት

**ዓላማ:-** የግል ንፅህና አጠባበቅ ዘዴዎችን መለየት

**መመሪያ:-** በቡድን በመወያየት መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ

**የመወያያ ጥያቄዎች:-**

1. የግል ንፅህና ምንድን ነው?

2. የግል ንፅህና አጠባበቅ ዘዴዎችን ዘርዝሩ።
3. በግል ንፅህና ጉድለት የሚከሰቱ በሽታዎችን ጥቀሱ።
4. ጤናማ እና የታመሙ ሰዎች የሚለዩበትን ባህሪያት ግለፁ።

ጤንነት ማለት የአንድ ሰው አካላዊ፣ አዕምሯዊ እና ማህበራዊ ደህንነት ማለት ነዉ። ሰዉ በአካሉና በአዕምሮዉ ላይ ምንም ህመም ከሌለዉ ጤነኛ ሰዉ ይባላል።ጤነኛ ለመሆን የግል ንፅህናን መጠበቅ አስፈላጊ ነዉ።

የግል ንፅህና ማለት ሰው ለሰውነቱ እና ለሚለብሰው ልብስ የሚያደርገዉ የንፅህና ጥንቃቄ ማለት ነው።

ንፅህና የሚጠብቅና የማይጠብቅ ልጅ



ሥዕል 2.6. የግል ንፅህናዉን የሚጠብቅና የማይጠብቅ ሰዉ ልዩነት

## 2.3.1. ንፅህናችንን ለምን እንጠብቃለን?

የግል ንፅህና መጠበቅ ራሳችንን ከበሽታ ለመከላከል፣ ንቁ ፣ ደስተኛና ጤነኛ ሆኖ ለመገኘት እና ሥራችንን በአግባቡ ለማከናወን ያስችለናል። የንፅህና ጉድለት ለተለያዩ የበሽታ ዓይነቶች የሚያጋልጥ ሲሆን ተፈጥሮአዊ

ውበታችንንም ይቀንሳል፡፡ስለዚህ የግል ንፅህናን መጠበቅ አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም የሚከተሉትን የግል ንፅህና መጠበቂያ መንገዶችን በመከተል የግል ንፅህናችንን እንጠብቃለን፡፡

**የግል ንፅህና መጠበቂያ መንገዶች:-**

- እጅን፣እግርን፣ፊትንና ፀጉርን በዉሃና በሳሙና መታጠብ
- የእጅና የእግርን ጥፍር መቁረጥ
- ገላን መታጠብ
- ጥርስን በሚገባ መፋቅ/መቦረሽ/
- ልብስን ማጠብና መተኮስ ወዘተ ናቸው፡፡



*ሥዕል 2.7 የግል ንፅህና መጠበቂያ ዘዴዎች*

## 2.3.2. የግል ንፅህና ጉድለት በሌሎች ሰዎች ላይ ምን ሊያስከትል ይችላል?

ከግል ንፅህና ጉድለት ከሚመጡ በሽታዎች አብዛኛዎቹ በቀላሉ ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰዉ የሚተላለፉ ናቸው፡፡ስለዚህ እኛ ንፅህናችንን ካልጠበቅንና በዚህም ምክንያት በተለያዩ ከግል ንፅህና ጉድለት በሚመጡ በሽታዎች ከተጠቃን

በሽታውን በቀላሉ ወደ ሌሎች ሰዎች ማስተላለፍ እንችላለን ማለት ነው።

**ለምሣሌ፡-** የዓይን ማዝ ከግል ንጽህና ጉድለት የሚመጣ በሽታና በዝንቦች አማካኝነት በቀላሉ ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰዉ የሚተላለፍ በሽታ ነው።

## 2.3.3. በንጽህና ጉድለት ምክንያት የሚከሰቱ በሽታዎች

### የተግባር 2.4: የቡድን ዉይይት

**ዓላማ፡-** የግል ንፅህና ጠቀሜታን መግለፅ

**መመሪያ፡-** በቡድን በመወያየት መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ

**የመወያያ ጥያቄዎች፡-**

1. በግል ንፅህና ጉድለት ምክንያት የሚመጡ በሽታዎችን ዘርዝሩ።
2. የግል ንፅህናዉን የማይጠብቅ ሰዉ ላይ የሚታዩትን ሁኔታዎች ግለፁ።

የግል ንጽህናችንን መጠበቅ ከሚሰጠን እርካታና ምቾት በተጨማሪ በግል ንጽህና እጥረት ከሚመጡ በሽታዎችም ይጠብቀናል።የግል ንጽህናችንን ካለመጠበቅ ከሚመጡ በሽታዎች መካከልም ጥቂቶቹ እንደ እከክ፣ የዓይንማዝ (ትራኮማ)፣ ተስቦ እና የወስፋት በሽታ ተጠቃሾች ናቸው።

## 2.3.4. ጤናማ እና የታመሙ ሰዎችን ማነፃፀር

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

በቤተሰባችሁ ውስጥ የታመመ ሰው ወይም ታሞ የሚያዉቅ ሰው አለ? ይህ ሰው በታመመ እና ጤነኛ በሆነ ጊዜ የሚያሳየው ፀባይ ተመሳሳይ ነው ወይስ ይለያያል? ልዩነቱን ግለፁ።

**የታመመ ሰው ፡-**

- ጥሩ ስሜት አይሰማውም
- አብዛኛዉ ጊዜዉን በመኝታ ያሣልፋል
- ቀልጣፋና ደስተኛ አይሆንም

- ሥራን በአግባቡ ሊሰራ አይችልም

ጤናማ ሰዉ

- ቀልጣፋና ፈጣን የሆነ
- ደስተኛና ጥሩ ስሜት የሚሰማው
- ጠንካራና የዕለት ተዕለት ተግባራዊ እንቅስቃሴ ላይ በንቃትና በብቃት ይሣተፋል




ሥዕል 2.8 ህመምተኛ እና ጤናማ ሰዉ

## 2.3.5. ለታመሙ ሰዎች ትኩረት እና እንክብካቤ መስጠት

### የተግባር 2.5: የቡድን ዉይይት

**ዓላማ:-** ለታመሙ ሰዎች የሚደረግ ትኩረት እና እንከብካቤ መንገዶችን መግለፅ

**መመሪያ:-** በቡድን በመወያየት መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ

**የመወያያ ጥያቄ:-**

- በቡድን በቡድን ሆናችሁ ከቤተሰቦቻችሁ አባላት አንዱ ቢታመም /ብትታመም/ ወይም አደጋ ቢደርስበት/ባት/ ምን አይነት እንክብካቤ እንደምታደርጉለት/ላት/ ተወያዩ::

ህመምተኝነት የውጫዊ ወይም የውስጣዊ ጤንነት መጓደል ነዉ፡፡በመሆኑም ህመምተኛ ሰው ፍላጎቶቹን ሁሉ ማሟላት አይችልም፡፡ስለዚህ ህመምተኛው ከእኛ የሚፈልገውን እንክብካቤ ማድረግ አለብን፡፡ይህ ሁኔታ በአንድ መልኩ ሰብአዊ ግዴታችን ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የመንፈስ እርካታን ይሰጠናል፡፡

**ለታመሙ ሰዎች ትኩረት እና እንክብካቤ መስጠት የሚቻልባቸዉ መንገዶች**

- የበሽታዉን ዓይነት መለየት
- የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ ማድረግ
- ማበረታታት
- ወደ ህክምና ቦታ መዉሰድ

ለህመምተኛዉ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ማቅረብ ለማሳሌ፡-መድሀኒት፣ ዉሀ ፣ ምግብ ወዘተ…



ሥዕል 2.9 ጤናማ ሰው ለህመምተኛዉ እርዳታ ሲያደርግ፡

## መልመጃ 2.3

ሀ. የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች ካነበባችሁ በኋላ ትክክል ከሆነ “እውነት”ትክክል ካልሆነ ደግሞ “ሀሰት” በማለት መልሱ፡፡

1. የታመመ ሰዉ የደስታ ስሜት አይታይበትም፡፡
2. ልብስን ማጠብና መተኮስ አንዱ የግል ንፅህና መጠበቂያ መንገድ ነዉ፡፡
3. ቀልጣፋና ንቁ አለመሆን የህመምተኛ ሰው ምልክት ነዉ፡፡

**ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ሆሄ በመምረጥ መልስ/ሽ/::**

1. በንፅህና ጉድለት የሚከሰት በሽታ ያልሆነዉ የቱ ነዉ?
   ሀ. የዓይን ማዝ
   ለ. የተስቦ በሽታ
   ሐ. የወስፋት በሽታ
   መ. የኤድስ በሽታ
2. ከሚከተሉት የጤናማነት መገለጫ ያልሆነዉ የቱ ነዉ?
   ሀ. ደስተኛ አለመሆን
   ለ. ጥሩ ስሜት መሰማት
   ሐ. ቀልጣፋ መሆን
   መ. በንቃትና በብቃት ሥራን ማከናወን

## 2.4. የቁስ አካላዊ ለውጦች



### መታወስ የሚገባቸው ቁልፍ ቃላት:-

☑ ቁስ
☑ አካላዊ ለዉጥ
☑ ሁነቶች
☑ ሙሙትሚሚ

### ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህን ንዑስ ርዕስ ተምራችሁ ስታጠናቅቁ:-

- ቁስ ምን እንደሆነ ትገልፃላችሁ::
- ቁስ አካላዊ ለውጦችን ትናገራላችሁ::
- የቁስ ሁነቶችን ትዘረዝራላችሁ::
- የሁነት ለዉጦችን ለማሳየት ቀላል ሙከራዎችን ታካሂዳላችሁ::

## የቁስ አካላዊ ለውጦች

### የተግባር 2.6: የቡድን ዉይይት

**ዓላማ፡-** በቁሶች ላይ የሚደረጉ አካላዊ ለዉጦችን መለየት

**መመሪያ፡-** በቡድን በመወያየት መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ

**የመወያያ ጥያቄዎች፡-**

1. ቁስ ምንድን ነው?
2. የቁስ አካላዊ ለዉጥ ምን ማለት ነዉ?
3. የቁስ አካላዊ ለዉጥ ባህርያትን ዘርዝሩ፡፡

## ቁስ

ማንኛውም በአካባቢያችን የሚገኝ ክብደት/መጠነ ቁስ/ ያለዉና ቦታ የሚይዝ ነገር ሁሉ ቁስ ይባላል፡፡ ለምሣሌ፡-ወንበር፣ጠረጴዛ፣አየር፣እፀዋት፣እንስሳትና ወዘተ…

ቁስ የተሠራዉ በአይን ከማይታዩ ጥቃቅን አቶሞች ነው፡፡ አቶሞች ሲጣመሩ ሞሌክዩልችን ይሆናሉ፡፡

ለምሣሌ፡-ሁለት የሃይድሮጅን አቶሞችና አንድ የኦክስጅን አቶም ሲጣመሩ ዉሃ ይፈጥራሉ፡፡

ቁስ የራሱ የሆነ ክብደትና ቦታ አለው፡፡ ለምሣሌ፡- አየርና ውሃ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ አየር በአይን የማይታይና በእጅ የማይዳሰስ ሊጨበጥ የማይችል ቁስ ነዉ፡፡

**ቁሶች በሶስት የተለያዩ ሁነቶች /State of matter / ይገኛሉ፡፡ እነሱም፡-**

1. **ጠጣር፡-** የራሱ የሆነ ቅርጽ እና ይዘት አለው፡፡

**ምሣሌ፡-** ብረት፣ወርቅ፣ጠረጴዛ፣ድንጋይ፣ወንበር ወዘተ…


2. **ፈሳሽ፡-** የራሱ የሆነ ቅርጽ የለውም ነገር ግን የራሱ የሆነ ይዘት አለው፡
   **ምሣሌ፡-** ውሃ፣ዘይት ወዘተ…
3. **ጋዝ፡-** የራሱ የሆነ ቅርጽ እና ይዘት የለውም፡፡ ምሣሌ፡- አየር

ቁስ አካል ሁለት አይነት መሰረታዊ ለውጦችን ያካሂዳል፡፡እነርሱም

ሀ) አካላዊ/ፊዚካላዊ/ ለውጥ እና

ለ) ንጥረ-ቁሳዊ ወይም ዉስጣዊ/ኬሚካላዊ / ለውጦች ይባላሉ፡፡ አካላዊ/ፊዚካላዊ/ ለውጥ

አዲስ ልዩ ቁስን ሊያስገኝ የማይችል ነገር ግን የቅርፅና መጠን ለዉጥ ሲኖረዉ አካላዊ/ፊዚካል/ለዉጥ ይባላል፡፡ ከዚህም ሌላ በነገሮች የሚከናወነው ለውጥ ዋናው ነገር /የዉስጥ ይዘቱ/ ሣይለወጥ በነበረበት የሚቆይበት ሂደት ነው፡፡ አካላዊ ለውጥ የሚያካትታቸው የሚከተሉት ናቸው፡፡ለምሳሌ:-የበረዶ መቅለጥ፣ የውሃ መፍላት፣ የጨው መሟሟት፣ የወረቀት በትንንሽ መቀደድ ወዘተ...




ሥዕል2.10.የቁስ አካል የሁነት ለውጥ

ተግባራዊ ክንዋኔ /ሙከራ/

የበረዶ መቅለጥ አካላዊ ለውጥ መሆኑን ለማሣየትና አካላዊ ለውጥን ለመረዳት የሚከተለውን ተግባራዊ ክንዋኔ በመሥራት አሳዩ

ለበረዶ መቅለጥ የሚያስፈልጉ ነገሮች:- ብርጭቆ እና በረዶ አሠራር


- መምህራችሁ በሚነግሩዋችሁ መሠረት በቡድን ትደራጃላችሁ
- የተወሰኑ ቡድኖች በረዶ ብርጭቆ ውስጥ በማድረግ የፀሐይ ሙቀት በሚገኝበት ሥፍራ በውጭ ያስቀምጣሉ፡፡

- ሌሎች ቡድኖች በረዶ ብርጭቆ ውስጥ በማድረግ የፀሐይ ሙቀትበማይደርስበት ክፍል ውስጥ ያኖራሉ፡፡
- መምህራችሁ ከሚነግሩዋችሁ ሰዓት በኋላ የተካሄደውን ለዉጥ ማየት፡ ፡ካያችሁት

ለዉጥ በመነሳት ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ በጽሁፍ አቅርቡ፡፡

1. የትኛው ቦታ ላይ የተቀመጠዉ በረዶ ቀድሞ በፍጥነት መሟሟት ጀመረ?
2. በበረዶዉና በሟሟዉ ውሃ መሃል ምን ልዩነት አለ?
3. ያያችሁት ለዉጥ ምን ዓይነት ለዉጥ ይባላል?

በአጠቃላይ በቁስ አካሎች ላይ የሚካሄድ የሁነት ለውጥ ቀጥሎ በተመለከተው መልክ ይገለፃል፡፡ አንድ ጥጥር በውሃ ወይም በሌላ ፈሳሽ ውስጥ የሚሟ እንደሆነ ድብልቁ ሙሙት ይባላል፡፡የሚሟሚው ጥጥር ሟሚ ሲባል ፈሳሹ ደግሞ አሟሚ ይባላል፡፡ስለዚህ ሟሚ (Solute) + አሟሚ (Solvent) →ሙሙት (Solution) አንዳንድ ነገሮች በውኃ ውስጥ ይሟሟሉ፡፡መሟሟት አካላዊ ለውጥ ነው፡ ፡ ምክንያቱም ሟሚ አካሉ የመጠን ለውጥ ስለሚያሳይ ነው፡፡ከዚያም በላይ ሙሙቱን ስናሞቅ ውኃ ተኖ የሟሟው ጥጥር በመያዣው ዕቃ ላይ ይቀራል፡፡



ሥዕል2.11.አሟሚ ሲተን ጥጥር/ሟሚው / በመያዣው እቃ ላይ ይቀራል

## 2.5. የብርሃን አስፈላጊነት

### የተግባር 2.7: የቡድን ዉይይት

**ዓላማ:-** ስለ ብርሃን ምንጭና ጥቅም መግለፅ

**መመሪያ:-** በቡድን በመወያየት መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ

**የመወያያ ጥያቄዎች:-**

1. ብርሃን ከምን ይገኛል?
2. የብርሃን ጥቅም ምንድን ነዉ?

ብርሃን ከተለያዩ የተፈጥሮና ሰዉ ሰራሽ ምንጮች ማግኘት ይቻላል:: ለምሳሌ:-ፀሀይ፣ ኤሌክትሪክ፣ ሻማና የማገዶ እንጨት ወዘተ…ናቸው:: ይሁንና ዋነኛዉ የብርሃን ኃይል ምንጭ ፀሀይ ናት::

ብርሃን ነገሮችን ለማየት፣ ለዕፀዋት ዕድገት፣ ለዕፀዋት ምግብ ዝግጅት፣ በተገቢዉ ሁኔታ ከቦታ ቦታ ለመንቀሳቀስና ወዘተ……ይጠቅማል::




ሥዕል 2.12 የብርሃን ምንጮች በከፊል

## መልመጃ 2.4

**ሀ. የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች ካነበባችሁ በኋላ ትክክል ከሆነ "እውነት" ትክክል ካልሆነ ደግሞ "ሀሰት" በማለት መልሱ፡፡**

1. አየር ቁስ አካል ነዉ፡፡
2. ፀሀይ የብርሃን ምንጭ ነዉ፡፡

**ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ሆሄ በመምረጥ መልስ/ሽ/፡፡**

1. ከሚከተሉት ዉስጥ ቁስ አካል ያልሆነዉ የቱ ነዉ?
   ሀ. ዉሃ　　　　ሐ. ሐይድሮጅን
   ለ. ድንጋይ　　　　መ. መልሱ የለም
2. ከሚከተሉት ዉስጥ አካላዊ ለዉጥ ያልሆነ የቱ ነዉ?
   ሀ. የሻማ መቅለጥ　　　　ሐ. የወረቀት መቃጠል
   ለ. የዉሃ ትነት　　　　መ. የወረቀት መቀደድ
3. ዉስን ቅርፅ የሌለዉና የተገኘዉን ቦታ የሚይዝ የቁስ አካላዊ ሁነት የትኛዉ ነዉ?
   ሀ.ጠጣር　　　　ሐ.ጋዝ
   ለ.ፈሳሽ　　　　መ.ለእናሐ መልስ ናቸዉ፡፡
4. ከሚከተሉት ዉስጥ አንዱ ከፈሳሽ ወደ ጋዝ የሚለወጥበት ሂደት ነዉ?
   ሀ. ቅልጠት　　　　ሐ.ዝልትነት
   ለ. ትነት　　　　መ. መልስ አልተሰጠዉም

# ማጠቃለያ

- ምግብ ለሰዉ ልጅ ከሚያስፈልጉ መሠረታዊ ፍላጎቶቻችን መካከል አንዱ ነዉ በመሆኑም ሰውና ሌሎች ህይወት ያላቸው ነገሮች ያለምግብ መኖር አይችሉም፡፡
- የተመጣጠነ ምግብ ከሁሉም የምግብ መደቦች የተለያዩ የምግብ ዓይነቶችን የያዘ ማዕድ ነው፡፡
- የምንመገባቸው የምግብ ዓይነቶች በአራት ዋና ዋና የምግብ ክፍሎች ይከፈላሉ፡፡እነዚህም የአትክልትና የፍራፍሬ ክፍል፣የእህልና ጥራጥሬ ክፍል፣የወተት ክፍል እና የሥጋ ክፍል ተብለዉ ይጠራሉ፡፡
- የምግብ መበከል ማለት ምግብ ለሰውነታችን የሚሰጠውን ጥቅም በተለያዩ ባዕድ ነገሮች ምክንያት መስጠት ሲያቋርጥና ለሰውነታችን ጎጂ ሲሆን ነው፡፡
- ጤንነት ማለት የአንድ ሰው አካላዊ፣ አዕምሯዊ እና ማህበራዊ ደህንነት ማለት ነው፡፡ጤነኞች ሁልጊዜ ደስተኞች፣ ነፃ፣ ከሰው ጋር ተግባቢ፣ ጠንካራና ንቁ በመሆን የዕለት ተዕለት ሥራቸውን በአግባቡ የሚያከናውኑ ናቸው፡፡
- የግል ንፅህና ማለት ሰው ለሰውነቱ እና ለሚለብሰው ልብስ የሚያደርገዉ ጥንቃቄ ማለት ነው፡፡የግል ንፅህና መጓደል ለተለያዩ የበሽታ ዓይነቶች የሚያጋልጥ ሲሆን ተፈጥሮአዊ ውበታችንንም ይቀንሳል፡፡በመሆኑም የግል ንፅህናን መጠበቅ አስፈላጊ ነው፡፡
- ከግል ንፅህና ጉድለት ከሚመጡ በሽታዎች አብዛኞዎቹ በቀላሉ ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰዉ የሚተላለፉ ናቸው፡፡
- ቁስ ማለት ማንኛውም በአካባቢያችን የሚገኝ ክብደት/መጠነቁስ/ ያለዉ ቦታ የሚይዝ ነገር ነዉ፡፡
- ቁሶች በሶስት የተለያዩ ሁነቶች /State of matter / ይገኛሉ፡፡እነሱም -ጠጣር፤ፈሳሽ እና ጋዝ ናቸዉ፡፡
- ብርሃን ነገሮችን ለማየት፣ ለዕፀዋት ዕድገት፣ በተገቢዉ ሁኔታ ከቦታ ቦታ ለመንቀሳቀስና ወዘተ......ይጠቅማል፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ የክለሳ ጥያቄዎች

### ሀ. የሚከተሉትን ጥቄዎች በማንበብ ትክክል ከሆነ “እዉነት” ትክክል ካልሆነ “ሐሰት” በማለት መልስ/ሽ/፡፡

1. የተመጣጠነ ምግብ በመመገብ በሽታን መከላከል ይቻላል፡፡
2. ጤናማ ሰዉ በዕዉቀቱም ሆነ በጉልበቱ ለሀገሩና ለወገኑ አለኝታ ነዉ፡፡
3. የግል ንፅህና መጠበቅ ከበሽታ ይከላከላል፡፡
4. ምግብ ለሰው ልጅ መኖርና ዕድገት አስፈላጊ ነው፡፡
5. ምግብ ከተመገብን በኋላ እጆቻችንን በዉሃና በሳሙና መታጠብ አለብን፡፡
6. የቅቤ መቅለጥ አካላዊ ለዉጥ ነዉ፡፡

### ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛዉን መልስ የያዘ ፊደል ምረጥ/ጭ/

1. ከሚከተሉት የምግብ ዓይነቶች ውስጥ ሰውነታችንን ለመገንባት የሚያገለግለው የትኛው ነው?
   - ሀ. እንጀራ
   - ለ. ወተት
   - ሐ. ሎሚ
   - መ. ብርቱኳን
2. ከሚከተሉት ውስጥ የምግብ ጥቅም ያልሆነው የቱ ነው?
   - ሀ. ሀይልና ሙቀት መስጠት
   - ለ. ሰውነት ማክሳትና ማቀጨጭ
   - ሐ. በሽታን መከላከል
   - መ. ሰውነትን ማፋፋትና መጠገን

### ሐ.ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛዉን መልስ ስጥ/ጭ/

1. የተበላሹ ምግቦች መለያ ምልክቶች ምን ምን ናቸው?
2. ምግብን የሚበክሉ ነገሮች ምንድን ናቸው?
3. የተመጣጠነ ምግብ መመገብ ጥቅሙ ምንድን ነው?
4. አካላዊ ለዉጥ ምንድን ነዉ?

# ምዕራፍ ሦስት

# የተፈጥሮ አካባቢ

ከምዕራፉ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች፡-

ተማሪዎች ይህን ርዕስ ተምራችሁ ስታጠናቅቁ፡-

- በአየር ሁኔታ እና በአየር ንብረት መካከል ያለውን ልዩነት ትለያላችሁ፡፡
- በተለያዩ ወቅቶች የምንጠብቀውን የአየር ሁኔታ ልዩነት ትገልጻላችሁ፡፡
- በዞናችሁ ዉስጥ ያለዉን የሙቀት ልዩነት ትገመግማላችሁ፡፡
- የዞናችሁን የዝናብ ስርጭት ታወዳድራላችሁ፡፡
- የዞናችሁን ዋና ዋና የአየር ንብረት መቆጣጠሪያዎችን ትለያላችሁ፡፡
- የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ ሀብቶችን ትገልጻላችሁ፡፡
- በዞናችሁ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶችን ትለያላችሁ፡፡
- የእያንዳንዱን የተፈጥሮ ሀብቶች አጠቃቀም እና እሴት ትገልጻላችሁ፡፡
- የተፈጥሮ ሀብት መመናመንን በመግለፅ በዞናችሁ የተፈጥሮ ሃብት የመበላሸት ዋና ዋና ምክንያቶችንና ውጤቶችን ትገልጻላችሁ፡፡
- በዞናችሁ ውስጥ የሀገር በቀል እና የተለመደው የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ እና የጥበቃ እርምጃዎችን ትገልጻላችሁ፡፡
- የተፈጥሮ ሀብቶችን የመጠበቅ እና የመንከባከብ አስፈላጊነት ለቀጣይ ትውልድ ፍላጎት ለማሟላት እሴትን ታዳብራላችሁ፡፡
- በትምህርት ቤታችሁ እና በወረዳችሁ ውስጥ የተፈጥሮ ሀብት ብክለትን ለመቀነስ እና እንደገና ጥቅም ላይ ለመዋል መንገዶችን ትጠቁማላችሁ፡፡

- በትምህርት ቤት እና በወረዳችሁ ውስጥ ተገቢያ ልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ አሰራሮች፣ተፅእኖዎችን እና ጥቅሞቹን ትጠቁማላችሁ፡፡

## በምዕራፉ የተካተቱ ይዘቶች

3.1. የዞናችን የአየር ንብረት

3.2. የተፈጥሮ ሀብት

3.3.በዞናችሁ ውስጥ ለመኖር እና ለልማት የተፈጥሮ ሀብቶች አስፈላጊነት

3.4.በትምህርት ቤታችሁ እና በወረዳችሁ ተገቢ እና ተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ልምዶች

3.5. ተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ልምዶች እና ውጤቶች

## መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ የተፈጥሮ አካባቢያችን ውስጥ ካሉ ዋና ዋና ነገሮች ዉስጥ ከፊሎቹን ትማራላችሁ፡፡ በምዕራፉ የሚተኮርበት ዋና የትምህርት ይዘት ስር የዞናችሁን የአየር ንብረት፣ የተፈጥሮ ሀብት፣ በዞናችሁ ውስጥ ለመኖር እና ለልማት የተፈጥሮ ሀብቶች አስፈላጊነት፣ በትምህርት ቤታችሁ እና በአካባቢያችሁ ተገቢ እና ተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ልምዶች እና ውጤቶች የሚሉ ዘርዘር ያሉ ጉዳዮችን ትማራላችሁ፡፡በዚህ ምዕራፍ የሚነሱ ዝርዝር ነጥቦች ከዕለት ተዕለት ኑሮአችሁ ጋር የተያያዙ በመሆናቸዉ በንቃት መከታተል እና ወደ ተግባር መተርጎም ይጠበቅባችኋል፡፡

## 3.1. የዞናችን የአየር ንብረት



### መታወስ የሚገባቸው ቁልፍ ቃላት፡-

- ☑ አየር ንብረት
- ☑ አየር ሁኔታ
- ☑ ከባቢ አየር

## ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

**ተማሪዎች ይህን ንዑስ ርዕስ ተምራችሁ ስታጠናቅቁ:-**

- በአየር ሁኔታ እና በአየር ንብረት መካከል ያለውን መሠረታዊ ልዩነት ትዘረዝራላችሁ::
- የአየር ንብረት አካላት ትገልጻላችሁ::
- የዞናችሁን የአየር ንብረት ትለያላችሁ::
- የአየር ንብረት ቁጥጥር አካላትን ትዘረዝራላችሁ::

## በንዑስ ርዕሱ የተካተቱ ይዘቶች

3.1.1.በአየር ሁኔታ እና በአየር ንብረት መካከል ያለው ልዩነት

3.1.2.የአየር ንብረት አካላት

3.1.3.የአየር ንብረት ቁጥጥር

## 3.1.1. በአየር ሁኔታ እና በአየር ንብረት መካከል ያለው ልዩነት

### የተግባር 3.1: የቡድን ዉይይት

**ዓላማ:-** የአየር ሁኔታ እና የአየር ንብረት ምንነትን መግለፅ

**መመሪያ:-** በቡድን በመወያየት መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ

**የመወያያ ጥያቄዎች:-**

1. የአየር ሁኔታ ማለት ምን ማለት ነው? የአየር ንብረትስ?
2. በአየር ሁኔታ እና በአየር ንብረት መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነዉ?
3. ስለአየር ሁኔታ እና አየር ንብረት ማወቅ ለምን ይጠቅማል?


### የአየር ሁኔታ ምንድን ነዉ?

የአየር ሁኔታ የአንድ የተወሰነ ቦታ ዕለታዊ የከባቢ አየር ሁኔታ ነው::የአየር ሁኔታ የአንድን አካባቢ የፀሐይ ብርሃን፣ ንፋስ፣ ትነት፣ እርጥበት፣ ደመና፣ ሙቀት፣ ወዘተ ያሉ ዕለታዊ የከባቢ አየር ሁኔታን የሚገልፅ ነው:: የአየር ሁኔታ በደቂቃዎች ወይም በሰዓታት ሊለዋወጥ ይችላል::

የአንድ የተወሰነ ቦታ የአየር ሁኔታ እንደሥራ፣ አመጋገብ፣ አለባበስ፣ መጓጓዣ /እንቅስቃሴ/፣ ግንኙነት፣ ግብርና፣ ወዘተ የመሳሰሉትን በዕለት ተዕለት የሰው

ሕይወት ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡

የአየር ሁኔታ እንደወቅቱ ይለያያል፡፡ ማለትም በበጋ፣በበልግ፣ በፀደይና በክረምት የሚኖረዉ የአየር ሁኔታ ልዩነት አለዉ፡፡



ፀሃያማ



ደመናማ



ዝናባማ

*ሥዕል 3.1 የተለያዩ ዕለታዊ የአየር ሁኔታዎች*

### የአየር ንብረት ምንድን ነዉ?

የአየር ንብረት ማለት በአንድ የተወሰነ አካባቢ የሚስተዋል የረጅም ጊዜ አማካይ የከባቢ አየር ሁኔታ ነዉ፡፡ የአንድ አካባቢ አየር ንብረት የአካባቢዉን ተፈጥሮአዊ ገፅታ ምን ሊመስል እንደሚችል ሊጠቁመን ይችላል፡፡ ለምሳሌ፡ -ቆላ፣ ወይናደጋ፣ ደጋ ወዘተ…

የአየር ንብረት በአንድ አካባቢ በኢንዱስትሪዎች ፣በግብርና፣ በተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ ገፅታዎች ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡

## 3.1.2. የአየር ንብረት አካላት

### የተግባር 3.2: የቡድን ዉይይት

**ዓላማ፡-** የአየር ንብረት አካላትን መለየት

**መመሪያ፡-** በቡድን በመወያየት መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ

**የመወያያ ጥያቄዎች፡-**

1. የአየር ንብረት አካላት ምንድን ናቸው?
2. የሙቀት መጠንና እርጥበት ያላቸዉ ግንኙነት ምንድን ነዉ?
3. የሙቀት መጠን ለምን ከቦታ ቦታ ይለያያል?

የአየር ንብረት አካላት ዉስጥ የሚካተቱት የሚከተሉት ናቸው:-

**የሙቀት መጠን:-** የሙቀት መጠን በአየር ውስጥ ያለው የሙቀት ኃይል መጠን ነው:: የመለኪያ አሃዱ ዲግሪ ሴልሺየስ ወይም ዲግሪ ፋራናይት ነው::

**ዝናብ:-** ዝናብ ከደመና ወደ ምድረ-ገጽ የሚወርድ ውሃ ነው::የዝናብ መጠን መለኪያ(ሬንጌጅ) በመጠቀም የዝናብን መጠን እንለካለን::

**እርጥበት:-** በአየር ውስጥ የተካተተው የውሃ ትነት ነው::መጠኑ በአካባቢዉ ባለው የዝናብ መጠን እና የፀሐይ ጨረር መጠን ይለያያል::

**የከባቢ አየር ግፊት:-** በከባቢ አየር ክብደት ምክንያት በተሰጠው ስፍራ ላይ የሚያሳድረዉ ኃይል ነው::

**ደመናነት:-** በከባቢ አየር ውስጥ ያሉት የደመናዎች ብዛት እንዲሁም የአየር ንብረት አካል ነው::

**ንፋስ:-** ንፋስ ማለት የሚንቀሳቀስ አየር ነው:: ይህም በአየር ግፊት ምክንያት ይፈጠራል::

**የፀሐይ ጨረር:-** ምንም እንኳን የማይታይ አካል ቢሆንም ሙቀትን ወደ ምድር በማቅረብ በአየር ንብረት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያሳድራል::

## 3.1.3. የአየር ንብረት ቁጥጥር

### የተግባር 3.3: የቡድን ዉይይት

**ዓላማ:-** የአየር ንብረት መቆጣጠሪያዎችን መለየት

**መመሪያ:-** በቡድን በመወያየት መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ

**የመወያያ ጥያቄዎች:-**

1. የአየር ንብረት ቁጥጥር ስንል ምን ማለታችን ነዉ?
2. ከምታዉቁት የአየር ንብረት መቆጣጠሪያዎች መካከል በአካባቢያችሁ
3. አየር ንብረት ላይ ከፍተኛ አስተዋፅዖ አለዉ የምትሉትን ጥቀሱ እና ተወያዩበት?

የዞናችን ወይም የአካባቢያችንን የአየር ሁኔታ የሚቀይሩ ወይም የሚወስኑ ምክንያቶች የአየር ንብረት መቆጣጠሪያዎች ተብለው የሚጠሩ ሲሆን ኬክሮስ፣ አየር ግፊት፣ የንፋስ ስርዓት፣ ከባህር ጠለል በላይ ያለዉ ከፍታ፣ የውቅያኖስ ሞገድ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

**የአየር ሙቀት፡-** የአየር ሙቀት ልዩነቶች የአንድን ቦታ ግፊት እና የንፋስ ስርዓት ይቆጣጠራሉ፡፡

ኬክሮስ፡- ከምድር ወገብ እና ከዋልታዎቹ አቅራቢያ ባለው የአየር ግፊቶች ልዩነቶች በዓለም አቀፍ የአየር ግፊት እና በንፋስ ስርዓቶች ላይ ተጽዕኖ ያስከትላል፡፡

ከባህር ጠለል በላይ ያለዉ ከፍታ፡- አንድ ቦታ ከባህር ጠለል በላይ ያለዉ ርቀት የቦታውን የአየር ንብረት የሚቆጣጠር ሌላው አስፈላጊ አካል ነዉ፡፡ በተጨማሪም የውሃ እና የአየር ዝውውር፣ የመሬት አቀማመጥና የመሳሰሉት የአየር ሁኔታ ሊቀይሩ የሚችሉ ምክንያቶች ናቸዉ፡፡

## መልመጃ 3.1

**ሀ. የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች አንብባችሁ ትክክል ከሆኑ "እዉነት" ትክክል ካልሆኑ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ፡፡**

1. በበጋና በክረምት ያለዉ የአየር ሁኔታ ተመሳሳይ ነዉ፡፡
2. የአየር ንብረት በአንድ አካባቢ የረጅም ጊዜ የከባቢ አየር ሁኔታ ነዉ፡፡
3. የፀሐይ ጨረር ሙቀትን ወደ መሬት በማቅረብ በአየር ንብረት ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡

**ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልስ/ሽ/፡፡**

1. ከሚከተሉት ዉስጥ በአየር ሁኔታ ሥር የሚካተተዉ የቱ ነዉ?
   - ሀ. ደመና
   - ሐ. የፀሐይ ብርሃን
   - ለ. ሙቀት
   - መ. ሁሉም መልስ ናቸዉ
2. በምድር ወገብ እና በዋልታዎች አቅራቢያ ባለዉ የአየር ግፊቶች ልዩነት ላይ ተፅዕኖ ያለዉ የቱ ነዉ?
   - ሀ. ኬኪሮስ
   - ሐ. ከፍታ
   - ለ. የአየር ሙቀት
   - መ. ሁሉም መልስ ናቸዉ

## 3.2. የተፈጥሮ ሀብት



### መታወስ የሚገባቸው ቁልፍ ቃላት:-

☑ ሰው ሰራሽ ሀብት
☑ የተፈጥሮ ሀብት
☑ ብክለት
☑ ታዳሽ
☑ መመናመን

### ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች:-

ተማሪዎች ይህን ንዑስ ርዕስ ተምራችሁ ስታጠናቅቁ:-

- የተፈጥሮ ሀብት ምንነትን ትገልጻላችሁ።
- የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ ሀብቶችን ትለያላችሁ፡
- በአካባቢያችሁ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶችን ትዘረዝራላችሁ።
- የተፈጥሮ ሀብቶችን ታዳሽና ታዳሽ ያልሆኑ በማለት ትመድባላችሁ።
- በአካባቢያችሁ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶችን ጥቅም ትዘረዝራላችሁ።
- የተፈጥሮ ሀብቶች መመናመን መንስዔዎችና የሚያሳድሩትን ተፅዕኖዎች ትገልፃላችሁ።

### የንዑስ ርዕሱ ይዘቶች

3.2.1.የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ ሀብቶች ትርጉም
3.2.2.በዞናችሁ ውስጥ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶች
3.2.3.በዞናችሁ ውስጥ የእያንዳንዱ የተፈጥሮ ሀብቶች አጠቃቀም እና እሴቶች

### የተግባር 3.4: የቡድን ዉይይት

**ዓላማ:-** የተፈጥሮ ሀብቶችን ምንነት መግለፅ

**መመሪያ:-** በቡድን በመወያየት መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ

**የመወያያ ጥያቄዎች:-**

1. የተፈጥሮ ሀብቶች ምንድን ናቸዉ?
2. ታዳሽና ታዳሽ ያልሆኑ የተፈጥሮ ሀብቶችን ዘርዝሩ።

አካባቢያችን በተለያዩ ሕይወት ባላቸውና ሕይወት በሌላቸው ነገሮች የተሞላ ነው፡፡የተፈጥሮ ሀብቶች የሚባሉት በተፈጥሮ የምናገኛቸዉና ለሰዉ ልጅ ጥቅም የሚዉሉ ናቸዉ፡፡የተፈጥሮ ሀብቶች ታዳሽ እና ታዳሽ ያልሆኑ ተብለው ይለያሉ፡፡ከሚታደሱት የተፈጥሮ ሀብቶች ውስጥ አፈር፣ ውሃ፣ አየር፣ ደንና የዱር እንስሳት ይገኙበታል፡፡ታዳሽ ያልሆኑ ከሚባለት የተፈጥሮ ሀብቶች እንደ ማዕድንና ነዳጅ ዘይት የመሳሰሉት ይገኙበታል፡፡

## 3.2.1. የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ ሀብቶች

### የተግባር 3.5: የቡድን ዉይይት

**ዓላማ፡-** የተፈጥሮና ሰዉ ሰራሽ ሀብቶችን መለየት

*መመሪያ፡-* በቡድን በመወያየት መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ

**የመወያያ ጥያቄዎች፡-**

1. የተፈጥሮና ሰዉ ሰራሽ ሀብቶች ልዩነት ግለፁ?
2. በአካባቢያችሁ የሚገኙ የተፈጥሮ እና ሰዉ ሰራሽ ሀብቶችን ዘርዝሩ፡፡

### የተፈጥሮ ሀብት

በምድር ላይ በተፈጥሮ የሚገኝ ማንኛውም ነገር የተፈጥሮ ሀብት ነው::የተፈጥሮ ሀብት የሰው ልጅ ፍላጎቶችን ሊያሟላ የሚችል ከአካባቢው የሚገኝ ማንኛውም ነገር ነው::የተፈጥሮ ሀብቶች ለሰው ልጅ ህልውና በጣም አስፈላጊ ናቸው::


ደን


ወንዝ


ማዕድን


የሜዳ አህያ


ዋልያ

ሥዕል 3.2 የተፈጥሮ ሀብቶች በከፊል

## ሰው ሰራሽ ሀብቶች

የሰው ልጅ ጣልቃ የሚገባበት፣ የሚያመነጨው፣ የሚያስተካክለው እና የሚቆጣጠራቸው ነገሮች ሁሉ ሰው ሰራሽ ሀብቶች በመባል ይታወቃሉ። በተፈጥሮ ዓለም ውስጥ የማይገኙ ነገር ግን ለሰው ሕይወት ዋጋ ያላቸው ነገሮች ሰው ሠራሽ ሀብቶች ተብለው ይገለፃሉ። ምሳሌ:-ወረቀት፣ ጎማ፣ ፕላስቲክ፣ ወዘተ ናቸው።

ሰው ሀብትን ለመፍጠር አስፈላጊውን ክህሎት እና ችሎታ አዳብሯል።ለምሳሌ፡ -ህንፃዎችን፣ማሽኖችን፣ ተሽከርካሪዎችን፣ ድልድዮችን፣ መንገዶችን ወዘተ ለመሥራት ብረቶችን፣ ሲሚንቶን፣ አሸዋን እና የፀሐይ ኃይልን ስንጠቀም ሰው ሰራሽ ሀብቶች ይሆናሉ።በተጨማሪም ቴክኖሎጂ ሰው ሰራሽ ሀብት ነው።


ህንፃዎች


ማሽኖች


ድልድይ


መንገድ

ሥዕል3.3. ሰው ሰራሽ ሀብቶች

## 3.2.2. በዞናችሁ ውስጥ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶች

### የተግባር 3.6: የቡድን ዉይይት

**ዓላማ:-** በዞናችሁ ዉስጥ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶች ከነጥቅማቸዉ መግለፅ

**መመሪያ:-** በቡድን በመወያየት መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ

**የመወያያ ጥያቄዎች:-**

1. በዞናችሁ ዉስጥ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶችን ከነጥቅማቸዉ ግለፁ።

የተፈጥሮ ሀብቶች የሚባሉት በተፈጥሮ የሚገኙና ለሰው ልጅ አገልግሎት የሚሰጡ ነገሮችን ሁሉ ያካትታል፡፡እነርሱም አፈር፣ አየር፣ ውሃ፣ ማዕድናት፣ የነዳጅ ዘይት፣ ዕፅዋት እና እንስሳት ወዘተ...ናቸው፡፡

## ማዕድናት

**ተማሪዎች! ማዕድን ምንድን ነው?**

ማዕድናት በመሬት (በከርሰ ምድር) ውስጥ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶች ሲሆኑ እነሱም፡ መዳብ፣ ብረት፣ ወርቅ፣ ብር፣ አሌሙኒየም፣ኮፐር ወዘተ ብረትነት ያላቸው ሲሆኑ ብረትነት የሌላቸው ደግሞ እንደተፈጥሮ ጋዝ፣ ነዳጅናዘይት የመሳሰሉት ናቸው፡፡

## አፈር

### የተግባር 3.7: የቡድን ዉይይት

**ዓላማ፡-** ስለ አፈር ጥቅም ይገልፃሉ

**መመሪያ፡-** በቡድን በመወያየት መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ

**የመወያያ ጥያቄዎች፡-**

1. አፈር ምንድን ነው?
2. የአፈር ጥቅም ምን እንደሆነ ዘርዝሩ፡፡

አፈር የመሬት የላይኛው ለስላሳው ክፍል ነው፡፡ አፈር በረጅም ዘመን ውስጥ ቀስ በቀስ ከድንጋይ እና ከሞቱት እንስሳትና ዕፀዋት ቅሪተ አካል የሚፈጠር የተፈጥሮ ሀብት ነው፡፡

## የአፈር ጥቅም

አፈር ለብዙ ነገሮች ይጠቅማል፡፡ ከጥቅሞቹም ጥቂቶቹ፡- ሰብል ለማምረት፣ ለግንባታና ለሸክላ ስራ ወዘተ...ናቸው፡፡

## ውሃ

### የተግባር 3.8: የቡድን ዉይይት

**ዓላማ:-** የውሃን ጥቅምና ምንጮች መለየት

**መመሪያ:-** በቡድን በመወያየት መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡

**የመወያያ ጥያቄዎች:-**

1. ውሃ ከምን ይገኛል?
2. ውሃ ለምን ጥቅም (አገልግሎት) እንደሚውል ጥቀሱ?

ውሃ ከሀይድሮጂን እና ከኦክስጅን ኬሚካል ንጥረ ነገሮች የተሰራ ነዉ፡፡ውሃ ለሰው ልጅ በዋነኛነት ከሚያስፈልጉ መሰረታዊ ነገሮች አንዱ ሲሆን አብዛኛውን የምድራችንን ክፍል የሚሸፍን የተፈጥሮ ሀብት ነው፡፡ውሃን ከተለያየ ምንጮች ልናገኝ እንችላለን፡፡

3. **የገፀ-ምድር ውሃ ለምሳሌ:-** ዝናብ፣ወንዝ፣ ኩሬ፣ሐይቅ፣ ባህር፣ ዉቅያኖስና ምንጭ የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡

1. የከርሰ-ምድር ውሃ **ለምሳሌ:-** የጉድጓድ ዉሀ

### የውሃ ጥቅም

- ውሃ ለሕይወት አስፈላጊ ነገር ነው፡፡ማለትም ህይወት ያላቸዉ ነገሮች በሙሉ ያለ ዉሀ መኖር አይችሉም፡፡
- ለቤት ዉስጥ ግልጋሎት(ለመጠጥ፣ ምግብ ለማብሰል፣ ለንፅህና) እንዲሁም ለእንስሳት በመጠጥነት ያገለግላል፡፡
- ለግብርና ስራ
- ለኢንዱስትሪና
- ለሀይል ማመንጫ ወዘተ ያገለግላል፡፡

## አየር

### ተማሪዎች! አየር ለምን ይጠቅመናል?

አየር ምድርን የከበበ በአይን የማይታይ የጋዞች ድብልቅ ነዉ፡፡

አየር ህይወትያላቸው ነገሮች ሁሉ ለመኖር የሚጠቀሙበት የተፈጥሮ ሀብት

ነው፡፡

ተማሪዎች! ሁሉም ሰዎች በየሰኮንዱ የሚተነፍሱት አየር መሆኑን ተገንዘባችሁ? ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ ሌሎች እንስሳትና ተክሎችም ጭምር ያለ አየር መኖር አይችሉም፡፡

**ደን**

## የተግባር 3.9: የቡድን ዉይይት

**ዓላማ፡-** ስለደኖች ጥቅም መግለፅ

**መመሪያ፡-** በቡድን በመወያየት መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡

**የመወያያ ጥያቄ፡-**

1. ደን ምን ጥቅም ይሰጣል?

ደን በአብዛኛው ከዛፎች የተመሰረተ ሆኖ ቁጥቋጦና ሣርን የሚያካትት ታዳሽ የተፈጥሮ ሀብት ነው፡፡

**የደን ጥቅሞች**

- አፈር እንዳይሸረሸር ይጠብቃል
- ለቤት ቁሳቁስ መሥሪያ ይሆናል
- ለቤት ግንባታ ይጠቅማል
- በማገዶነት ያገለግላል
- የምግብ ምንጭ ነው
- ለዱር እንስሳት መጠለያ እና የመሳሰሉት የደን ጥቅሞች ናቸዉ፡፡





ሥዕል 3.4 የደን ጥቅሞች በከፊል

## የዱር እንስሳት

ተማሪዎች! የዱር እንስሳት ሲባል ምን ማለት ነው? የምታዉቋቸዉን የዱር እንስሳት ስም ለመምህራችሁ ንገሩ።

የዱር እንስሳት ከትናንሽ ነፍሳት አንስቶ እስከ ግዙፍ እንሰሳት ድረስ ያሉትን በመሬት ላይና በውሃ ውስጥ በዱር የሚኖሩ እንስሳት ሁሉ የሚያጠቃልል ነው። የዱር እንስሳት ለማዳ እንስሳት አይደሉም።




ሥዕል 3.5 የዱር እንስሳት በከፊል

**የዱር እንስሳት ጥቅሞች**

- ለገቢ ምንጭነት፡- ጎብኝዎችን በመሳብ እና የአካል ክፍሎቻቸዉን በመሸጥ የገቢ ምንጭ ያስገኛሉ፡፡ለምሳሌ፡- ጥርሳቸዉ እና ቆዳቸዉ
- አንዳንድ የዱር እንስሳት ለመድሃኒት መሞከሪያና ለምርምር ይውላሉ፡፡
- የዱር እንስሳት በፈቃድ እየታደኑ ለምግብነት ያገለግላሉ፡፡
- የዱር እንስሳት ጥርስ፣ ቀንድ እና ቆዳም ጌጣጌጦችን ለመስራት ያገለግላሉ፡፡
- ውብና ልዩ አፈጣጠር ያላቸው አዕዋፍት ቀለማቸውና ባህሪያቸው ሲታይ የደስታ ስሜት የሚሰጡ ናቸው፡፡

## 3.2.3. በዞናችሁ ውስጥ የእያንዳንዱ የተፈጥሮ ሀብቶች አጠቃቀም እና እሴቶች

**የተግባር 3.10: የቡድን ዉይይት**

**ዓላማ፡-** የዞናችሁን የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ዘዴ መለየት

**መመሪያ፡-** በቡድን በመወያየት መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ

**የመወያያ ጥያቄዎች፡-**

1. የዞናችሁ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ዘዴ ምን ይመስላል?

የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ማለት የተፈጥሮ ሀብቱን ደህንነት ሳንጎዳው አገልግሎቱ ዘላቂና አስተማማኝነት ባለው መንገድ ለቀጣዩም ትውልድ ሊተላለፍ በሚያስችል ዘዴ ሣይባክን መጠቀም ማለት ነዉ፡፡

**የተፈጥሮ ሀብት ለማህረሰባችን ብዙ ጥቅሞችን ይሰጣል፡፡ጥቂቶቹን ቀጥለን እንመለከታለን፡-**

- ሰፋ ያለ የኢንዱስትሪ ቁሳቁስ፣ ከእፅዋት እና ከእንስሳት፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለምርትነት ያገለግላሉ
- ለሕክምና
- ሀብቶች ለማንኛውም ሀገር ዕድገት አስፈላጊ ናቸው፡፡ለምሳሌ፡- ኃይል

ለማመንጨት፣ ለኢንዱስትሪ ልማት የማዕድን ሀብቶችን እንፈልጋለን።

- ከተፈጥሮ ሀብቶች አጠቃቀም ጋር የተዛመዱ ዘርፎች ሥራን ይሰጣሉ ወዘተ…

## መልመጃ 3.2

### ሀ. የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች አንብባችሁ ትክክል ከሆኑ "እዉነት" ትክክል ካልሆኑ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ።

2. የተፈጥሮ ሀብቶች የሰዉን ልጅ ፍላጎት የሚያሟሉ ሀብቶች ናቸዉ።
3. የዱር እንስሳት ለማዳ እንስሳት ናቸዉ።
1. አየር በአይን የማይታይ የተለያዩ ጋዞች ድብልቅ ነዉ።

### ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልስ/ሽ/።

1. ሰዉ ሰራሽ ሀብት ያልሆነዉ የቱ ነዉ?

   ሀ. ሕንፃ ሐ. ማሽን

   ለ. ደን መ. ተሽከርካሪ

2. ከሚከተሉት ዉስጥ የዉሃ ጥቅም የሆነዉን ለዩ

   ሀ. ለመጠጥ ሐ. ለመጓጓዣ

   ለ. ለእፀዋት ዕድገት መ.ሁሉም መልስ ናቸዉ

### ሐ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ስጡ

1. ከማዕድናት ዉስጥ የተወሰኑትን ዘርዝሩ።
2. ከደን ጥቅም ቢያንስ ሦስቱን ጥቀሱ።

## 3.3. በዞናችሁ ውስጥ ለመኖር እና ለልማት የተፈጥሮ ሀብቶች አስፈላጊነት

### ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች:-

ተማሪዎች ይህን ንዑስ ርዕስ ተምራችሁ ስታጠናቅቁ:-

- የተፈጥሮ ሀብቶችን የመጠበቅ እና የመንከባከብ አስፈላጊነት ለቀጣይ ትውልድ ፍላጎት ለማሟላት እሴትን ታዳብራላችሁ።
- የእያንዳንዱን የተፈጥሮ ሀብቶች አጠቃቀም እና እሴት ትገልጻላችሁ።

- የተፈጥሮ ሀብት መመናመንን በመግለፅ በዞናችሁ የተፈጥሮ ሃብት የመበላሸት ዋና ዋና ምክንያቶችንና ውጤቶችን ትገልጻላችሁ፡፡
- በዞናችሁ ውስጥ የሀገር በቀል እና የተለመደው የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ እና የእንክብካቤ እርምጃዎችን ትገልጻላችሁ፡፡
- የተፈጥሮ ሀብቶችን የመጠበቅ እና የመንከባከብ አስፈላጊነት ለቀጣይ ትውልድ ፍላጎት ለማሟላት እሴትን ታዳብራላችሁ፡፡
- በትምህርት ቤታችሁ እና በወረዳችሁ ውስጥ የተፈጥሮ ሀብት ብክለትን ለመቀነስ እና እንደገና ጥቅም ላይ ለመዋል መንገዶችን ትጠቁማላችሁ፡፡

## የተግባር 3.11: የቡድን ዉይይት

**ዓላማ፡-** የዞናችሁን የተፈጥሮ ሀብት እሴቶችን መለየት

**መመሪያ፡-** በቡድን በመወያየት መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ

**የመወያያ ጥያቄዎች፡-**

1. በአካባቢያችሁ ያሉ የተፈጥሮ ሀብቶች ለምን አገልግሎት ይዉላሉ?

የተፈጥሮ ሀብቶች ለሰው ልጅ ከሚያበረክቱት ጠቀሜታዎች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡ እነሱም፡-

- ለምግብ ምንጭነት
- ለልብስ
- ለመጠለያ
- ለገቢ ምንጭነት
- ለመጓጓዣ
- ለመዝናኛ
- ለቱሪስት መስህብነት (የሀገር ገጽታን ለማሳደግ)
- ግብርና
- ንግድ
- የተለያዩ የመገልገያ ቁሳቁሶችንና ጌጣጌጦችን ለመስራት፣ወዘተ...

### 3.3.1. በዞናችሁ የተፈጥሮ ሀብት የመመናመን፣ የመበላሸት መንስኤዎች እና ውጤቶች

**የተግባር 3.12: የቡድን ዉይይት**

**ዓላማ:-** የዞናችሁን የተፈጥሮ ሀብት ጉዳት መንስኤ እና ዉጤቶችን መለየት

**መመሪያ:-** በቡድን በመወያየት መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ

**የመወያያ ጥያቄዎች:-**

1. የተፈጥሮ ሀብት መመናመን ማለት ምን ማለት ነዉ?
2. በዞናችሁ ያሉ የተፈጥሮ ሀብቶች መመናመን መንስኤዎችን ጥቀሱ?
3. በዞናችሁ ያሉ የተፈጥሮ ሀብቶች መመናመን ዉጤቶችን ዘርዝሩ?

የተፈጥሮ ሀብት መመናመን ማለት የተፈጥሮ ሀብቶችን በአግባቡ ባለመጠቀም እንዲባክኑ ወይም እንዲበላሹና በይዘትም እንዲቀንሱ ማድረግ ነዉ።

**ከዋነኞቹ የተፈጥሮ ሀብት ጉዳቶች ዉስጥ የሚካተቱት:-**

- የአየር ብክለት
- የዉሃ ብክለት
- የደን መጨፍጨፍ
- የአፈር መሸርሸር ናቸዉ።

**የአየር ብክለት**

የአየር ብክለት ማለት የከባቢ አየር ይዘት መዛባት እንዲሁም በከባቢ አየር ውስጥ መኖር የማይገባቸው ለሰው ልጅ ጤንነት ተስማሚ ያልሆኑ ጋዞች ወደ ከባቢ አየር ውስጥ መቀላቀል ማለት ነው።

**የአየርብክለት መንስኤዎች**

- ከፋብሪካዎች የሚለቀቁ መርዛማነትያላቸው የጭስ ጋዞች

**ለምሣሌ:-** ሰልፈርዳይኦክሳይድ

- ከተሽከርካሪ ሞተር የሚለቀቅ በከፊል የተቃጠለ ጋዝ

**ለምሳሌ:-** ካርቦንሞኖክሳይድ

- ከመፀዳጃ ቤቶች የሚለቀቅ ጋዝ

**ለምሳሌ፡-** ሚቴን ጋዝ

- በቤት ውስጥ ከሚነዱ እንጨትና ከሰል የሚለቀቅ ጭስ

**ለምሳሌ፡-** ካርቦንዳይኦክሳይድ

- የደን ቃጠሎና የደን መጨፍጨፍ ናቸው፡፡

## የአየር ብክለት የሚያስከትላቸዉ ጉዳቶች

የአየር ብክለት፣ ራስ ምታት፣ ማዞር እና የማቅለሽለሽ ስሜት ሊያስከትል ይችላል፡፡እንዲሁም የረዥም ጊዜ የጤና ችግሮች ማለትም የልብ ህመምና እንደ ሳንባ ካንሰር ያሉ የመተንፈሻ አካላት በሽታዎችን እንዲከሰቱ ሊያደርግ ይችላል፡፡የአየር ብክለት በሰዎች ነርቭ፣ አንጎል፣ ኩላሊት፣ ጉበት እና ሌሎች አካላት ላይ የረጅም ጊዜ ጉዳት ሊያስከትል ይችላል፡፡



*ሥዕል 3.6.ከፋብሪካዎች የሚለቀቁ አየርን የሚበክሉ የተቃጠሉ ጋዞች*

## የውሃ ብክለት

ውሃ በአግባቡ ካልተያዘ በቀላሉ ይበከላል፤ለጤና ጠንቅ የሆኑ ተህዋሲያንም መራቢያ ይሆናል፡፡ የተበከለ ውሃ ደግሞ ለሰውም ሆነ በውስጡ ለሚኖሩ እንስሳት እና እፅዋት አደገኛ ነው፡፡

## የውሃ ብክለት መንስኤዎች፡-

- ከፋብሪካዎችና ሆስፒታሎች ወደ ወንዞችና ሀይቆች የሚለቀቁ እጣቢ ጋዞች፣ዝቃጭና ኬሚካሎች

- ከሽንት ቤት ውጪ መፀዳዳት
- ከመኖሪያ ቤቶችና ሆቴሎች የሚወገድ ጥራጊ ቆሻሻ
- ከእርሻ መሬት በጎርፍ አማካኝነት እየታጠበ ወደ ወንዞችና ሀይቆች የሚገባ የማዳበሪያ ኬሚካል ወዘተ ናቸው፡፡

## የውሃ ብክለት የሚያስከትላቸዉ ጉዳቶች

የተበከለ ውሃ መጠቀም ለውሃ ወለድ በሽታ መዛመት መነሻ ስለሚሆን ውሃን ከብክለት መጠበቅ ተገቢ ነው፡፡የውሃ ብክለት እንደታይፎይድ፣ ኮሌራ፣ ሄፓታይተስ እና ሌሎች የተለያዩ በሽታዎችን ያስከትላል፡፡

## የደን መመናመን

ለደን ሀብት መመናመን መንስኤዎች ሁለት ናቸው፡፡እነሱም:- የሰደድ እሳትና የደን መጨፍጨፍ ናቸው፡፡ለደን ሀብት ደህንነት የሚረዱ ዘዴዎችም ከሰደድ እሳት መጠበቅ፣ በክፍት ቦታዎች ሁሉ ተክሎችን መትከል፣ ደንን አለመቁረጥና በተቆረጠው ምትክ ሌላ መትከል ተጠቃሾች ናቸው፡፡

## የደን መመናመን የሚያስከትላቸዉ ጉዳቶች:-

- የዛፎች እና ሌሎች እፅዋት መጥፋት
- የዱር አራዊቶች መሰደድ
- የአየር ንብረት ለውጥ እና በረሃማነት
- የአፈር መሸርሸርን እና የምርት መቀነስ
- ጎርፍን ያስከትላል
- በከባቢ አየር ውስጥ የአየር ብክለት የሚያስከትሉ ጋዞችን መጨመር እና ሌሎች በርካታ ችግሮችን ሊያስከትል ይችላል፡፡

## የአፈር መሸርሸር

የአፈር መሸርሸር ማለት የአፈር ላይኛው ክፍል በጎርፍና በንፋስ እየታጠበና እየተጠረገ መወሰድ ማለት ነው፡፡

## የአፈር መሸርሸር ዋና መንስኤዎች

- የደን መጨፍጨፍ
- የግንባታ እና የመዝናኛ እንቅስቃሴዎች

- ኃይለኛ ንፋስ በሚነፍስበት ጊዜ የላይኛው አፈር በንፋስ መወሰድ
- በተራራማ ቦታዎች ላይ ዝናብ ሲዘንብ አፈሩ ይታጠባል
- ከመጠን በላይ ለግጦሽ መጠቀም ወዘተ....

የአፈር መሸርሸር የሚያስከትላቸዉ ጉዳቶች፡-

- የአፈር ለምነት መቀነስ
- በጅረቶችና በወንዞች ውስጥ ብክለት እና ደለል እንዲጨምር ያደርጋል
- አሳን ጨምሮ ዉሀ ዉስጥ በሚኖሩ እንስሳት ላይ ተፅዕኖ ይኖረዋል
- የተራቆቱ መሬቶች ብዙውን ጊዜ ውሃ የመያዝ አቅማቸው አነስተኛ ነው፤ ይህም ጎርፍን ሊያባብስ ይችላል።

## 3.3.2. በዞናችሁ የሀገር በቀል እና መደበኛ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና የጥበቃ እርምጃዎች

### የተግባር 3.13: የቡድን ዉይይት

ዓላማ፡- በዞናችሁ የሀገር በቀል እና መደበኛ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና የጥበቃ እርምጃዎችን መለየት

መመሪያ፡- በቡድን በመወያየት መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ

የመወያያ ጥያቄዎች፡-

1. በዞናችሁ በመደበኛነት የተፈጥሮ ሀብት እንዴት ይጠበቃል?
2. በዞናችሁ የሀገር በቀል የተፈጥሮ ሀብት አጠባበቅ ምን ይመስላል?

የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ማለት የተፈጥሮ ሀብትን ለብክነትና ለጉዳት ከሚዳርጉ ሁኔታዎች መጠበቅ፣ መከላከልና መንከባከብ ማለት ነው። የተፈጥሮ ሀብቶቻችንን ተገቢውን ጥበቃና እንክብካቤ ሳናደርግለት በግድ የለሽነት ከተጠቀምንባቸው ለጉዳት ይዳረጉና ሙሉ በሙሉ ሊጠፉ ይችላሉ። ነገር ግን በጥንቃቄና በእንክብካቤ ይዘን ከተጠቀምንባቸው ዘላቂና አስተማማኝ አግልግሎት ይሰጡናል።

በአካባቢያችን በተናጥልም ሆነ ከህብረተሰቡ ጋር በጋራ የሚተዳደሩ የተፈጥሮ ሀብቶችን መልሶ ለማቋቋም እና ለመጠበቅ የረጅም ጊዜ እርምጃዎችን በንቃት

እንዲተገበሩ እና የኑሮ ዘይቤዎችን ዘላቂ ልማት እንዲኖረዉ ለማስቻል ሁለንተናዊ የተፈጥሮ ሀብት አጠባበቅ በባህላቸዉ ዉስጥ ሲተገብሩ ቆይተዋል። ሰዎች የተፈጥሮ ሀብትን ለመጠበቅ በመደበኛና ሀገር በቀል የሆኑ መንገዶችን ይጠቀማሉ።

**ከሀገር በቀል የተፈጥሮ ሀብት የጥበቃ እርምጃዎች ውስጥ ጥቂቶቹ:-**

- በቂ የመኖሪያ ቦታ መከለል
- ደንን አለመጨፍጨፍ
- የግጦሽና እርሻ ቦታን መከለልና በአግባቡ መጠቀም
- እርከን በመስራት
- የቤት እንስሳት ስምሪት መወሰን
- በአካባቢዉ ባህላዊ የደን አጠባበቅ ዘዴዎች እና የመሳሰሉት ናቸዉ።

**ከመደበኛ የተፈጥሮ ሀብት የጥበቃ እርምጃዎች ውስጥ ጥቂቶቹ:-**

- ህገ-ወጥ አደንን ማቆም
- ሁለም ዜጋ ለዱር እንሰሳት ጥበቃ እንዲያደርግ ማስተማር
- ደንን ማልማት
- የዱር እንስሳትን መጠለያ አካባቢ መከለልና አስፈላጊውን ጥበቃማድረግ፣ **ለምሳሌ:-** ፓርኮችን ማቋቋም
- ደን ያለአግባብ አለመጨፍጨፍ፣ የዛፍ ተከላ በአካባቢው ላይ በየጊዜው ማካሄድ
- የደን ቃጠሎን መቆጣጠር
- ዘመናዊ አስተራረስ ዘዴዎችን መጠቀም
- ሕብረተሰቡን ማስተማር እና ግንዛቤ ማስጨበጥ
- በጣም የተጎዱ አካባቢዎችን ከሰዉ እና ከእንስሳት ንክኪ መጠበቅ የመሳሰሉት መደበኛ የተፈጥሮ ሀብት የጥበቃ እርምጃዎች ውስጥ የሚካተቱ ናቸዉ።

### 3.3.3. በዞናችሁ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና የጥበቃ ጥቅሞች

#### የፕሮጀክትሥራ

**ዓላማ፡-** በዞናችሁ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና የጥበቃ ጥቅሞችን መለየት

**መመሪያ፡-** በአካባቢያችሁ ወደሚገኘው የተፈጥሮ ሃብት ጥበቃ ጽሕፈት ቤት ሄዳችሁ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባለሙያን በመጠየቅ ያጠናቀራችሁትን ሪፖርት ለመምህራችሁ እና ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ፡፡

1. በአጠቃላይ በዞናችሁ ወይም በአካባቢያችሁ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ዘዴ ምን ይመስላል? (ዘዴዎቹ፣ የህብረተሰቡ ተሳትፎ፣ በጎ ልምዶችን ያካተተ ቢሆን)
2. ከመምህራችሁና ከትምህርት ቤታችሁ ማህበረሰብ ጋር በመመካከርና በማቀድ ለአካባቢው ማህበረሰብ አርአያ ሊሆን የሚችል ችግኝ የማፍላት፣ የመትከልና የመንከባከብ ተግባራዊ እንቅስቃሴዎችን አከናዉኑ፡፡

ተፈጥሮ ለዕለታዊ ፍላጎቶቻችን ሁሉንም አስፈላጊ ነገሮች ይሰጠናል፡፡ በሕዝብ ብዛት እና በሰው ቸልተኝነት ምክንያት የተፈጥሮ ሀብቶቻችንን ከመጠን በላይ በመበዝበዝ ላይ ይገኛል፡፡ ይህ ከቀጠለ ለመጪው ትውልዳችን የሚቀር ሀብት የለም፡፡ በመሆኑም የተፈጥሮ ሀብትን መጠበቅ ብዙ ጥቅሞች ይኖሩታል፡፡

**የተፈጥሮ ሀብትን የመጠበቅ ጥቅም፡-**

- ሥነ-ምህዳራዊ ሚዛንን ለመጠበቅ
- መጪዉ ትውልድ ሀብቶቹን ማግኘት መቻሉን ለማረጋገጥ
- ብዝሃሕይወትን ለመጠበቅ
- ለአየር ንብረት ለውጥ የመቋቋም ችሎታን ለመገንባት
- የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ
- የውሃ ጥራትን ለመጠበቅ
- የመሬት ገጽታዎችን እና የመዝናኛ መገልገያዎችን ለመንከባከብ
- የሰው ልጅ ለመኖር የሚያስፈልጉትን መሠረታዊ ነገሮች ማለትም
- ኦክስጅንን፣ ሙቀትን፣ ነዳጅን፣ የፀሐይ ኃይልን እና የመሳሰሉትን

- ይሰጣል።
- የዕለት ተዕለት ሕይወታችንን በብዙ መንገድ ያቀልልናል።በአጠቃላይ
- ያለ የተፈጥሮ ሀብቶች ሕይወትን መምራት አንችልም።

## መልመጃ 3.3

### ሀ. የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች አንብባችሁ ትክክል ከሆኑ "እዉነት" ትክክል ካልሆኑ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ።

1. የተፈጥሮ ሀብቶች የአካባቢን የአየር ንብረት ሚዛን ለመጠበቅ ይረዳሉ።
2. ከተሽከርካሪዎች የሚለቀቁ የተቃጠሉ ጋዞች አየርን አይበክሉም።
3. የአፈር መሸርሸር የመሬትን ለምነት ይቀንሳል።

### ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልስ/ሽ/።

1. ከሚከተሉት የተፈጥሮ ሀብት መመናመን መንስኤ የሆነዉ የቱ ነዉ?

   ሀ. ብክለት　　　ሐ. የደን መጨፍጨፍ

   ለ.የአፈር መሸርሸር　　　መ.ሁሉም መልስ ናቸዉ

2. የአየር ብክለት የጤና ጉዳት የሆነዉ የቱ ነዉ?

   ሀ. የሳንባ ምች　　　ሐ.ማቅለሽለሽ

   ለ.ራስ ምታት　　　መ.ሁሉም መልስ ናቸዉ

## 3.4. ተገቢና ተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ልምዶች

### ከንዐስ ርዕሱ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች:-

ተማሪዎች ይህን ንዑስ ርዕስ ተምራችሁ ስታጠናቅቁ:-

1. በአካባቢያቸዉ የሚታዩ ተገቢና ተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድልምዶችን ትለያላችሁ።
2. በትምህርት ቤታችሁ እና በአካባቢያችሁ ውስጥ ተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ዘዴዎችን ትጠቁማላችሁ።

## የተግባር 3.14: የቡድን ዉይይት

**ዓላማ፡-** ተገቢና ተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ልምዶችን መለየት

**መመሪያ፡-** በቡድን በመወያየት መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ

**የመወያያ ጥያቄዎች፡-**

1. በአካባቢያችሁ ተገቢ የቆሻሻ አወጋገድ ልምዶች ናቸዉ የምትሏቸዉን ዘርዝሩ፡፡
2. በት/ቤታችሁና በአካባቢያችሁ የታዘባችሁትን ተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ልምዶችን ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩ፡፡
3. የከተማዉን ማዘጋጃ ቤት ወይም በምትኖሩበት ቀበሌ የሚመለከተዉን ባለሙያ ጠይቃችሁ የቆሻሻ አወጋገድ ልምዶችን ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

### ተገቢ የቆሻሻ አወጋገድ ልምዶች

ተገቢ የቆሻሻ አወጋገድ ልምዶች የሚባሉት የተለያዩ ዓይነት ቆሻሻዎችን በመለየት በጤናና በአካባቢ ላይ ጉዳት ሳያደርስ በአግባቡ ማስወገድ ማለት ነዉ፡፡ እነዚህም ልምዶች የሚከተሉት ናቸዉ፡፡

- ቆሻሻን በየቦታዉ አለመጣልና ለቆሻሻ መጣያ በተዘጋጁ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ዕቃዎች መጠቀም
- ደረቅ ቆሻሻን ሰብስቦ በቆሻሻ ማስወገጃ ጉድጓድ ዉስጥ ማስወገድና ማቃጠል
- በየቦታዉ የሚሰበሰቡና የሚጠራቀሙ ቆሻሻዎችን ቶሎ ቶሎ ማስወገድ
- ደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻዎችን ለይቶ ማስወገድ
- በየሜዳዉ አለመፀዳዳትና ሽንት ቤት መጠቀም
- ሊበሰብስ የሚችልና ሊበሰብስ የማይችል ቆሻሻ (እንደፔስታል፣ ፕላስትክ የመሳሰሉት) በመለየት ማስወገድ
- በግቢያችንም ሆነ በአካባቢያችን የሚገኙትን ወደ ብስባሽነት (ፍግ ወይም ኮምፖስት) መለወጥና ለጓሮ አትክልት በማዳበሪያነት መጠቀም ወዘተ….



ሀ. ሊበሰብሱ የሚችሉ ቆሻሻዎች



ለ. ሊበሰብሱ የማይችሉ ቆሻሻዎች

ሥዕል 3.7. ሊበሰብሱ የሚችሉ እና ሊበሰብሱ የማይችሉ ቆሻሻዎች

## ተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ልምዶች

- ቆሻሻን በየቦታዉ መጣል
- የቆሻሻ መጣያ ጉድጓድ አለመጠቀም
- የፈሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦይ ወይም ቱቦ አለመጠቀም
- ቆሻሻን በቆሻሻ ማጠራቀሚ ዕቃዎች አለማስቀመጥ
- ደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻዎችን ለይቶ አለማስወገድ ወዘተ...

## መልመጃ 3.4

### ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ስጥ/ጭ/

በሚከተለዉ ሰንጠረዥ ዉስጥ ሦስት ተገቢ የቆሻሻ አወጋገድ ልምዶችንና ሦስት ተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ልምዶችን ዘርዝር/ሪ/፡፡

| ተ.ቁ | ተገቢ የቆሻሻ አወጋገድ ልምዶች | ተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ልምዶች |
|---|---|---|
| 1. | | |
| 2. | | |
| 3. | | |

## 3.5. ተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ልምዶች እና ዉጤቶች

### ከንዕስ ርዕሱ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች:-

ተማሪዎች ይህን ንዑስ ርዕስ ተምራችሁ ስታጠናቅቁ:-

1. በዞናችሁ (በአካባቢያችሁ) ተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ልምዶችን ትዘረዝራላችሁ፡፡
2. በዞናችሁ (በአካባቢያችሁ) ተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ልምዶች የሚያስከትሉትን ተፅዕኖዎች ትገልፃላችሁ፡፡

ተገቢ ያልሆነ የቆሻሻ አወጋገድ ማለት የተለያዩ ዓይነት ቆሻሻዎችን በአግባቡ አለመለየትና ለይቶ አለማስወገድ ሲሆን ፤ይህም ጤናንና አካባቢን ለጉዳት የሚዳርግ ተግባር ነዉ፡፡

### የተግባር 3.15: የቡድን ዉይይት

**ዓላማ:-** ተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ልምዶች እና ዉጤቶች መለየት

**መመሪያ:-** በቡድን በመወያየት መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ

**የመወያያ ጥያቄዎች:-**

1. በዞናችሁ (በአካባቢያችሁ)ተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ልምዶችን ዘርዝሩ፡፡
2. በዞናችሁ (በአካባቢያችሁ) ተገቢ ባልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ልምዶች የሚያስከትለዉን ተፅዕኖዎች ግለፁ?

በግቢያችንም ሆነ በአካባቢያችን ቆሻሻን በተገቢዉ መንገድ አለማስወገድና ተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ልምዶችን ማዳበር በሕብረተሰቡና በአካባቢያችን ላይ የሚያስከተሏቸዉን ዉጤቶች የሚከተሉት ናቸዉ:-

- በሽታ አምጪ ተህዋስያንና ዝንቦች እንዲራቡበትና በሽታን እንዲያስከትሉ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል
- ለአየር ብክለት(ቆሻሻን ሰብስበን ስናቃጥል አየር በካይ ጋዞች እንደ ካርበንዳይኦክሳይድ ያሉ ጋዞች አየሩን በመበከል የተለያዩ ጤና ችግሮችን እንዲፈጠር ምክንያት ይሆናል)

- በግቢያችንና በአካባቢያችን መጥፎ ሽታ ያመጣል
- ወንዞችን በመበከል በተጠቃሚው ህብረተሰብ እና እንስሳት እንዲሁም ዕፀዋት ላይ ጉዳት ያስከትላል፡፡
- የጎርፍ መዉረጃ ቱቦና ቦይ በመዝጋት የጎርፍ አደጋ እንዲከሰትና መንገድ እንዲበላሽ ያደርጋል
- የአካባቢያችንን በጎ ገፅታ ወይም ዉበት ያበላሻል
- የማይበሰብሱ ቆሻሻዎች እንደፕላስቲክ ያሉት ዕፀዋት ሥሮቻቸዉን አፈር ዉስጥ እንዳይሰዱና እንዳያድጉ አስተዋፅኦ ያደርጋሉ




ሥዕል 3.8 ተገቢ ያልሆነ የቆሻሻ አወጋገድ

## ማጠቃለያ

- የአየር ሁኔታ የአንድን አካባቢ የፀሐይ ብርሃን፣ ንፋስ፣ ትነት፣ እርጥበት፣ ሙቀት፣ ወዘተ ያሉ ዕለታዊ የከባቢ አየር ሁኔታ ነው።
- የአየር ንብረት ማለት በአንድ የተወሰነ አካባቢ የሚስተዋል የረጅም ጊዜ አማካይ የከባቢ አየር ሁኔታ ነዉ።
- የዞናችን ወይም የአካባቢያችንን የአየር ሁኔታ የሚቀይሩ ወይም የሚወስኑ ምክንያቶች የአየር ንብረት መቆጣጠሪያዎች ተብለው የሚጠሩ ሲሆን እነዚህም ኬክሮስ ፣ አየር ግፊት እና የንፋስ ስርዓት ፣ ከባህር ጠለል በላይ ያለዉ ርቀት ፣ የውቅያኖስ ሞገድ እና የመሳሰሉት ናቸው።
- የተፈጥሮ ሀብቶች የሚባሉት በተፈጥሮ የምናገኛቸዉና ለሰዉ ልጅ ጥቅም የሚዉሉ ናቸዉ።
- የሰው ልጅ ጣልቃ የሚገባበት፣ የሚያመነጨው፣ የሚያስተካክለው እና የሚቆጣጠራቸው ነገሮች ሁሉ ሰው ሰራሽ ሀብቶች በመባል ይታወቃሉ።
- የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ማለት የተፈጥሮ ሀብቱን ደህንነት ሳንጎዳው አገልግሎቱ ዘላቂና አስተማማኝነት ባለው መንገድ ለቀጣዩም ትውልድ ሊተላለፍ በሚያስችል ዘዴ ሣይባክን መጠቀም ማለት ነዉ።
- የተፈጥሮ ሀብት መመናመን ማለት የተፈጥሮ ሀብቶችን በአግባቡ ባለመጠቀም እንዲባክኑ ወይም እንዲበላሹ በይዘትም እንዲቀንሱ ማድረግ ነዉ፡
- በየአካባቢዉ የተለያዩ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና ልምዶች ይኖራሉ።
- ተገቢ የቆሻሻ አወጋገድ ልምዶች የሚባሉት የተለያዩ ዓይነት ቆሻሻዎችን በመለየት በአግባቡ ማስወገድ ማለት ነዉ።

## የምዕራፉ ማጠቃለያ መልመጃ/ የክለሳ ጥያቄዎች/

### ሀ. የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች አንብባችሁ ትክክል ከሆኑ "እዉነት" ትክክል ካልሆኑ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ፡፡

1. የአየር ንብረት ዕለታዊ የአየር ሁኔታ ነዉ፡፡
2. ማዕድናት ሰዉ ሰራሽ የተፈጥሮ ሀብቶች ናቸዉ፡፡
3. ከቤታችን የሚወገዱ ቆሻሻዎችን በየቦታዉ መጣል ተገቢ አይደለም፡፡

### ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልስ/ሽ/፡፡

1. የአየር ንብረት አካል የሆነዉ የቱ ነዉ?
   - ሀ. ዝናብ
   - ለ. እርጥበት
   - ሐ. ንፋስ
   - መ. ሁሉም መልስ ናቸዉ
2. ከሚከተሉት የማይታደስ የተፈጥሮ ሀብት የቱ ነዉ?
   - ሀ. ማዕድን
   - ለ. ደን
   - ሐ. አፈር
   - መ.አየር
3. የተፈጥሮ ሀብት ጥቅም የሆነዉ የቱ ነዉ?
   - ሀ. ለምግብነት
   - ለ. ለመዝናኛ
   - ሐ. ለቱሪስት መስህብነት
   - መ.ሁሉም መልስ ናቸዉ
4. የአፈር መሸርሸር መንስኤ ያልሆነዉ የቱ ነዉ?
   - ሀ. የደን መጨፍጨፍ
   - ለ. የአየር ብክለት
   - ሐ. ከመጠን በላይ ግጦሽ
   - መ. አዉሎ ንፋስ

### ሐ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጥ/ጭ/

1. የአየር ንብረት ምን እንደሆነ ግለፁ፡፡
2. የተፈጥሮ ሀብት መመናመን ዉጤት ግለፁ፡፡
3. ተገቢና ተገቢ ያልሆነ የቆሻሻ አወጋገድ ማለት ምን ማለት ነዉ?

# ምዕራፍ አራት

# ማህበራዊ አካባቢ

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች!ይህን ምዕራፍ በሚገባ ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- የባህል ምንነትን ትገልፃላችሁ።
- በዞናችሁ ያሉትን የተለያዩ ባህላዊ ልምዶችን ትገልጻላችሁ።
- በዞናችሁ ዉስጥ የሚነገሩ ቋንቋዎችን ትለያላችሁ።
- በዞናችሁ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና ለጥበቃ አስፈላጊ የሆኑ ባህላዊ አሠራሮችን ትለያላችሁ።
- የባህል ብዝሃነትን በኪነጥበብ ታደንቃላችሁ።
- በዞናችሁ ውስጥ የአየር ንብረት በባህል ላይ ያለውን ተጽዕኖ ትገልጻላችሁ፡ ፡
- በዞናችሁ ዋና ዋና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችን ታብራራላችሁ።
- በዞናችሁ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች በተፈጥሮ ሀብቶች ላይ የሚያሳድሩትን አሉታዊ ተፅእኖ ትለያላችሁ።
- ግብይትን ትተረጉማላችሁ።
- በዞናችሁ የተፈጥሮ ሀብትን እና የምርቶቻቸውን የግብይት ልምዶችን ትገልጻላችሁ።
- በዞናችሁ ውስጥ የመጓጓዣ ሁኔታን ትገልጻላችሁ።

## መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ ሥር የባህል ትርጓሜ፣ ልምድ፣ በዞናችሁ ያሉትን የተለያዩ አለባበስ፣ አመጋገብና የግጭት አፈታት፣ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችን፣ የተፈጥሮ ሀብት ፣ግብይትና ለግብይት የሚቀርቡ ምርቶች እና የመጓጓዣ መንገዶችን ትማራላችሁ፡፡ በግል፣ በጥንድ እና በቡድን እየሆናችሁ በዉይይት መማር ይጠበቅባችኋል፡፡

## 4.1. የባህል ብዝሃነት

### መታወስ የሚገባቸው ቁልፍ ቃላት:-

- ☑ ባህል
- ☑ ባህላዊ ልምዶች
- ☑ የባህል ብዝሃነት
- ☑ ግብይት
- ☑ መጓጓዣ
- ☑ ኢኮኖሚ

### በምዕራፉ የተካተቱ ንዑስ ይዘቶች

4.1.1. ባህል እና ባህላዊ ልምዶች ትርጓሜ እና ምሳሌዎች

4.1.2. የተለያዩ ባህሎች በዞናችሁ (አለባበስ ፣አመጋገብ ፣የግጭት አፈታት ወዘተ)

4.1.3. በዞናችሁ የሚገኙ ቋንቋዎች

4.1.4. በዞናችሁ ለተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ አስፈላጊ ባህላዊ ልምዶች

4.1.5. በዞናችሁ ዋና ዋና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች

4.1.6. የተለያዩ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች በዞናችሁ የተፈጥሮ ሀብት ላይ ያለዉ አሉታዊ ተፅዕኖዎች

4.1.7. የግብይት ትርጓሜ

4.1.8. በዞናችሁ ለገበያ የሚቀርብ የተፈጥሮ ሀብት እና ምርቶቻቸው

4.1.9. በዞናችሁ የተፈጥሮ ሀብት እና ምርቶቻቸው የግብይት ልምዶች

4.1.10. ለሰዉ እና ሸቀጦች የተለያዩ የመጓጓዣ መንገዶች

## 4.1.1. ባህል እና ባህላዊ ልምዶች ትርጓሜ እና ምሳሌዎች

### ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ! ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፡-

- ባህል ምን እንደሆነ ትገልጻላችሁ፡፡
- በዞናችሁ ያሉትን የተለያዩ ባህላዊ ልምዶችን ትጠቅሳላችሁ፡፡
- በዞናችሁ ለተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና ለጥበቃ አስፈላጊ የሆኑ ባህላዊ አሠራሮችን ትለያላችሁ፡፡
- የባህል ብዝሃነትን በኪነጥበብ ታደንቃላችሁ፡፡
- በዞናችሁ ውስጥ የአየር ንብረት በባህል ላይ ያለውን ተጽዕኖ ትገልጻላችሁ፡፡

### የተግባር 4.1: የቡድን ዉይይት

**ዓላማ፡-** የባህል ብዝሃነትን መግለፅ

**መመሪያ፡-** በቡድን በመወያየት መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ

**የመወያያ ጥያቄዎች፡-**

1. ባህል ምንድነዉ?
2. ስለባህል ብዝሀነት እና ባህላዊ ልምዶች የምታዉቁትን ጥቀሱ፡፡

**የሚና ጨዋታ፡-**

**ዓላማ ፡-** የባህል ብዝሃነትን በኪነጥበብ መግለፅ፡፡

**መመሪያ፡-** በቡድን በቡድን በመሆን በአካባቢያችሁ የሚታወቁትን የባህል ብዝሃነትን የሚያንፀባርቁ ጭዉዉቶችን ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

ባህል የአንድ የተወሰነ ማህበረሰብ ወይም የሰዎች ሀሳቦች፣ እምነቶች፣ ልምዶች ፣ ጥበባት እና ማህበራዊ ባህሪዎች ጥምረት ነው፡፡ ባህል የአንድ ህብረተሰብ ማንነት መገለጫ ነው፡፡ ስለዚህ ባህል ቋንቋን፣ ሃይማኖትን፣ ምግብን፣ ማህበራዊ ልምዶችን፣ ሙዚቃን እና ጥበቦችን ያካተተ የአንድ

ወይም የተወሰኑ ሰዎች የቡድን ባህሪያት እና ዕውቀት ነው።

ባህል በተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች መካከል የሚፈጠር የተግባቦት ዘይቤ ነዉ።ይህ ዘይቤ በማህበረሰቡ ዉስጥ በጎ ሥነ ምግባር ያላቸዉ የጋራ እሴቶች፣ እምነቶች፣ ፅንሰ ሀሳቦችን ይወሰናል ። በዚሁ ዘይቤ አሰራር ዉስጥ ግለሰቦች የሚወጡት ኃላፍነትና የሚያከናዉኑት ተግባር ይኖራቸዋል።

የባህል ብዝሃነት በአንድ ማህበረሰብ ዉስጥ የተለያዩ ባህል መኖሩን የሚገልፅና አንዳቸው የሌላውን ልዩነት ማክበርን ሊያመለክት ይችላል።

የሚከተሉት ባህላዊ ልምዶች በምሳሌነት ይጠቀሳሉ፡-

- ሃይማኖታዊ እና መንፈሳዊ ልምዶች
- የአለባበስ ልምዶች
- ባህላዊ የሕክምና ልምዶች
- የጥበብ መግለጫ ዓይነቶች
- የአመጋገብ ሥርዓት እና የምግብ አሰራር ልምዶች፤
- የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ
- የቤት አሰራር
- የሕፃናት እንክብካቤ ልምዶች
- አስተዳደርና አመራር
- የግጭት አፈታት
- የዕለት ተዕለት ሕይወት ልምዶች (የቤተሰብ ግንኙነቶችን ጨምሮ) ወዘተ…

## 4.1.2. የተለያዩ ባህሎች በዞናችሁ

### የተግባር 4.2: የቡድን ዉይይት

**ዓላማ:-** በዞናችሁ የተለያዩ ባህላዊ ተግባራትን መለየት

**መመሪያ:-** በቡድን በመወያየት መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ።

**የመወያያ ጥያቄዎች:-**

**ተማሪዎች! በዞናችሁ ዉስጥ ያሉትን የተለያዩ ባህላዊ ልምዶች ከታላላቆቻችሁ/ ሽማግሌዎች/ በመጠየቅ ክፍል ዉስጥ ለክፍል ጓደኞቻችሁና ለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡**

ሰዎች በአካባቢያቸው ያለው አመለካከት በአብዛኛው የሚመነጨው በልዩ ልዩ ባህላቸው እና በባህላዊ ልምዶቻቸው ነው፡፡ በአንድ አካባቢ የተለያዩ ባህላዊ ክንዉኖች ይፈጸማሉ፡፡ ከእነዚህም ባህላዊ ክንዉኖች መካከል አለባበስ፣ አመጋገብ እና የግጭት አፈታት ወዘተ.. የተወሰኑት ናቸዉ፡፡


## ባህላዊ አመጋገብ

ባህላዊ አመጋገብ ከምግብ አዘገጃጀት ጀምሮ የምግቡን አቀራረብ፣ የምግብ ማቅረብያ ባህላዊ ዕቃዎችን እንዲሁም የአመጋገብ ስርዓትን ሁሉ ያጠቃልላል፡ ፡ ባህላዊ ምግቦች በአብዛኛዉ የሚዘጋጁት ከአካባቢያቸዉ ከሚገኙ የምግብ ምንጮች ነዉ፡፡

## ባህላዊ አለባበስ

ባህላዊ አለባበስ ማለት የአንድን የተወሰነ ማህበረሰብ ባህል ወይም ማንነት ለመወከል ጥቅም ላይ የሚዉል የባህል መገለጫ ልብስ ነዉ፡፡ ይህም የአንድ አካባቢ እሴቶችን እና ባህላዊ ቅርስን ለመጠበቅ እና የሕዝቦችን የአንድነት ስሜት በመፍጠር ረገድ ወሳኝ ተምሳሌታዊ ሚና ይጫወታል፡፡ በአብዛኛዉ ባህላዊ አለባበስ የማህበረሰቡን የአኗኗር ሁኔታ እና የሚኖሩበትን የአካባቢ አየር ሁኔታን ያገናዘበ ነዉ፡፡





ሥዕል 4.1.ከባህላዊ ልብሶች በከፊል

## ባሕላዊ የግጭት አፈታት

ባህላዊ የግጭት አፈታት ማለት በአንድ ማህበረሰብ ዉስጥ በግለሰብ ደረጃም ይሁን በቡድን የሚፈጠሩ ግጭቶችን ወይም አለመግባባቶችን ለመፍታት የሚረዳ በፅሁፍ ወይም በሰነድ ያልተቀመጠ ሆኖም ግን በማህበረሰቡ ዘንድ የሚተገበር ህግና ደንብ ነዉ። በዚህ የግጭት አፈታት ስልት ጥፋተኛን የሚያስተካክል ወይም የሚያስተምር እና ዳግም ወደ ጥፋት እንዳይገባ ቃል የሚገባበት ሥርዓት ነዉ።

ባህላዊ የግጭት አፈታት የተለያዩ ዘዴዎች እና ሂደቶች አሉት። እነዚህም ድርድር፣ ሽምግልና፣ የግልግል ዳኝነትና የመሳሰሉት ይገኙበታል።



ሥዕል 4.2.ባህላዊ የግጭት አፈታት

### የተግባር 4.3: የቡድን ዉይይት

**ዓላማ:-** በአካባቢያችሁ ያሉ ባሕላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎችን መለየት

**መመሪያ:-** በቡድን በመወያየት መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ

**የመወያያ ጥያቄዎች:-**

1. በአካባቢያችሁ የግጭት መነሻ የሆኑ ነገሮችን ዘርዝሩ።
2. በአካባቢያችሁ ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎችን ጥቀሱ።

የሚና ጨዋታ :-

**ዓላማ :-** ባህላዊ የግጭት አፈታትን በኪነጥበብ መግለፅ

**መመሪያ:-** በቡድን በቡድን በመሆን በአካባቢያችሁ የሚታወቁትን ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎችን በጭዉዉት መልክ ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

## 4.1.3. በዞናችሁ የሚገኙ ቋንቋዎች

### የተግባር 4.4: የቡድን ዉይይት

**ዓላማ:-** በዞናችሁ የሚገኙ ቋንቋዎችን መለየት

**መመሪያ:-** በቡድን በመወያየት መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ።

**የመወያያ ጥያቄዎች:-**

1. ቋንቋ ምንድን ነዉ?
2. የቋንቋ ጠቀሜታን ዘርዝሩ።
3. ቋንቋ ከባህል ጋር ያለዉን ቁርኝት ግለፁ።
4. በዞናችሁ የሚነገሩ ቋንቋዎችን ዘርዝሩ።

ቋንቋዎች የሰዎች ቀዳሚ የመግባቢያ ዘዴዎች ናቸው። ቋንቋ ለሰው ልጅ ግንኙነት ወሳኝ አካል ነው። ቋንቋዎች በንግግር፣ በምልክት ወይም በጽሁፍ ሊተላለፉ ይችላሉ። ብዙ ቋንቋዎች የራሳቸዉ ድምጾች፣የፅሁፍ ምልክቶች(ፊደላት) እና የአጻጻፍ ስርዓት አላቸው። ቋንቋ ጥያቄ ለመጠየቅ ፣ ለጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ፣ሀሳቦችን እና ፍላጎቶችን ለማስተላለፍ እና የሌሎችን አገላለጽ እና ስሜት ለመረዳት ይረዳል። ቋንቋ ሰዎች እርስ በርስ የሚግባቡበት፣ ግንኙነት የሚፈጥሩበት እና የማህበረሰብ ስሜት የሚፈጥሩበት መንገድ ነው። መግባባት የማንኛውም ማህበረሰብ ዋና አካል ሲሆን ቋንቋም የዚያ አስፈላጊ ገጽታ ነው። ቋንቋ የባህል ወሳኝ አካል ነው ምክንያቱም ሰዎች የባህል እሴቶቻቸዉን፣ እምነቶቻቸዉን እና ልማዶቻቸዉን ለማስተላለፍ የሚጠቀሙበት መንገድ ነው። ባህል እና ቋንቋ የማይነጣጠሉ ናቸው። መጀመሪያ ቋንቋ ካልተማርን

ባህልን መረዳት አንችልም:: ከአንድ ማህበረሰብ ጋር በቋንቋቸዉ ስትግባቡ ከቋንቋ ተናጋሪው ባህል ጋር ትገናኛላችሁ:: በአንድ አካባቢ ወይም ዞን የተለያዩ ቋንቋዎች ሊነገሩ ይችላሉ :: እያንዳንዱ ብሄረሰብ የተለየ ባህላዊ ልምዶች እና በብሄሩ የተለየ ቋንቋ ይናገራል:: እንዲሁም በአንድ አካባቢ ዉስጥ የሚኖሩ ማህበረሰቦች የተለያየ ቋንቋ መቻል የቋንቋ ብዝሀነትን ያመጣል::

## 4.1.4. በዞናችሁ ለተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ አስፈላጊ ባህላዊ ልምዶች

### የተግባር 4.5: የቡድን ዉይይት

**ዓላማ:-** በዞናችሁ ለተፈጥሮ ጥበቃ አስፈላጊ ባህላዊ ልምዶች ግለጹ

**መመሪያ:-** በቡድን በመወያየት መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ::

**የመወያያ ጥያቄ:-**

1. በአካባቢያችሁ(በዞናችሁ)ያሉትን ባህላዊ የተፈጥሮ ሀብት አጠባበቅ ልምዶችን ዘርዝሩ::

የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ማለት የተፈጥሮ ሀብትን ለብክነትና ለጉዳት ከሚዳርጉ ሁኔታዎች መጠበቅ፣ መከላከልና መንከባከብ ማለት ነው::

የተፈጥሮ ሀብቶች ውስን እና ዘላቂነት በሌለው አጠቃቀም ሊጠፉ የሚችሉ ስለሆነ በአካባቢያችሁ የሚዘወተሩ ባህላዊ የተፈጥሮ አጠባበቅ ልምዶች ሊበረታቱ ይገባል:: ለምሳሌ:- የእርከን ሥራ፣ የደን አጠባበቅ፣ የአስተራረስ ዘዴ ወዘተ...በተለያዩ አካባቢዎች የሚዘወተሩ ባህላዊ የተፈጥሮ አጠባበቅ ልምዶች ናቸዉ::

## 4.1.5. በዞናችሁ ዋና ዋና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች

### የተግባር 4.6: የቡድን ዉይይት


**ዓላማ :-** በዞናችሁ ዋና ዋና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችን መለየት

**መመሪያ:-** በቡድን በመወያየት መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ

## የየመወያያ ጥያቄዎች:-

1. ቤተሰቦቻችሁ በምን ሥራ ይተዳደራሉ?
2. በዞናችሁ ወይም በአካባቢያችሁ ያሉትን ዋና ዋና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችን ጥቀሱ።

በአንድ አካባቢ(ዞን) የሚኖሩ ማህበረሰቦች በተለያዩ የምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴዎች ላይ ይሰማራል።ከእነዚህም ውስጥ ግብርና(እርሻ)፣ እንዱስትሪ፣ ማዕድን ቁፋሮ፣ ንግድ፣ ትራንስፖርትና ቱሪዝም ዋና ዋናዎቹ ናቸው። በተጨማሪም ሰዎች ለመኖርና በኢኮኖሚ ራሳችዉን ለመደገፍ በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ላይ ይሰማራሉ።




ሥዕል 4.3 ሰዎች በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ላይ ተሰማርተዉ

### ግብርና

## የተግባር 4.7: የቡድን ዉይይት

ዓላማ:-የግብርናን ጥቅም መለየት

መመሪያ:-በቡድን በመወያየት መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ

የመወያያ ጥያቄዎች:-

1. ግብርና ምንድን ነው?
2. የግብርናን ጠቀሜታ አብራሩ።

ግብርና ማለት አዝርዕትና የእንስሳት እርባታን በአንድነት የሚያጠቃልል የምጣኔ ሀብት ዘርፍ ነው።ግብርና ለሀገራችን ኢኮኖሚ መሰረት ነው።በአሁኑ ጊዜ አብዛኛዉ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚተዳደረው በግብርና ነዉ።ማለትም ሰብልን በማምረትና እንስሳትን በማርባት ነው።

የሰብል ምርት ከግብርና ዘርፎች አንዱና ዋነኛው ነው።ዋነኞቹ የሰብል አይነቶች ስንዴ፣ ገብስ፣ ጤፍ፣ ማሽላ፣ በቆሎ፣ ባቄላ፣ ሽንብራ፣ ምስርና ሌሎች ናቸው። ከእነዚህ በተጨማሪ የቅባት እህሎችና እንደ ቡና ያሉ የግብርና ውጤቶችም ይመረታሉ።


የእንስሳት እርባታ የቀንድ ከብቶች፣የጋማ ከብቶች እና የዓሣ እርባታ የመሳሰሉትን የሚያካትት ሲሆን በአብዛኛው በአርብቶ አደሩ አካባቢ የሚከናወን የግብርና መተዳደሪያ ነዉ።

## ኢንዱስትሪ

ኢንዱስትሪ ማለት የተለያዩ የግብርና፣ የደንና የማዕድን ዉጤቶችን በጥሬ ዕቃነት በመጠቀም የሰዉ ኃይልና ዘመናዊ መሳሪያዎችን ተገልግለዉ ወደ ሌላ የተሻሻለ ምርትነት የመለወጥ ሂደት ነዉ። ምሳሌ፡- ቆዳን በመጠቀም ወደ ጫማነት መለወጥ

እንዱስትሪ በተለያዩ የሥራ ዘርፍ ለተሰማሩ ግለሰቦችም ሆነ ለሀገራችን ጠቃሚ የምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴ ነው። እንዱስትሪ በሁለት ይከፈላል።

1. **የጎጆ እንዱስትሪ፡-** የተለያዩ የዕደጥበብ ስራዎችን ያጠቃልላል። የዕደ ጥበብ ስራዎች በአብዛኛው የእጅ መሣሪያዎችን በመጠቀም የሚሰሩ ናቸዉ። ለምሳሌ፡- የሽመና ስራ፣ የሸክላ ስራ፣ የብረታ ብረት ስራ፣ የቆዳ ስራ፣የጌጣጌጥ ስራና የመሳሰሉት ናቸው።



ሥዕል 4.3 ሀ.የሽመና ሥራ



ለ.የሸክላ ሥራ

1. **ዘመናዊ እንዱስትሪ፡-** ዘመናዊ ኢንዱስትሪ የሚባሉት በነዳጅ ወይም በኤሌክትሪክ ሀይል በሚንቀሳቀሱ ማሽኖች እና ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች የሚከናዉኑና በአጭር ጊዜ ብዙ ምርት ማምረት የሚችሉ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡- ፋብሪካዎች



ሥዕል 4.5 ፋብሪካ

**የተግባር 4.8: የቡድን ዉይይት**

**ዓላማ፡-** የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በተፈጥሮ ሀብት ላይ ያለዉን ተፅዕኖ መግለፅ

**መመሪያ፡-** በቡድን በመወያየት መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ

**የመወያያ ጥያቄ፡-**

1. በአካባቢያችሁ የሚከናወኑ የስራ እንቅስቃዎች በተፈጥሮ ሀብት ላይ ያላቸዉን አዎንታዊና አሉታዊ ተፅዕኖዎችን ግለፁ፡፡

## 4.1.6. የእኮኖሚ እንቅስቃሴ በተፈጥሮ ሀብት ላይ ያለዉ ተፅዕኖ

የተፈጥሮ ሀብት በምርት ሂደት ውስጥ የኢኮኖሚ ዕድገትን የሚያነቃቃ ቁልፍ ግብዓት ነው፡፡ እርሻ፣ ኢንዱስትሪና ኮንስትራክሽን (ግንባታ) የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ መሰረት የሚያደርገዉ ከተፈጥሮ ሀብት ከሚገኙ ዉጤቶች ላይ በመሆኑ የተፈጥሮ ሀብት መመናመንን ያስከትላሉ፡፡ ከነዚህም ጥቂቶቹ፡- የደን መጨፍጨፍ፣ በረሃማነት፣ የአፈር መሸርሸር፣ የነዳጅ ዘይት መቀነስና አየርን የሚበክሉ ጋዞች መጠን መጨመር ናቸዉ፡፡

## 4.1.7. የግብይት ትርጓሜ

### የተግባር 4.9: የቡድን ዉይይት

**ዓላማ:-** የግብይት ትርጓሜን ማብራራት

**መመሪያ:-** በቡድን በመወያየት መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ

**የመወያያ ጥያቄዎች:-**

1. ግብይት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ግለፁ::
2. በምትኖሩበት አካባቢ ያሉትን የግብይት ሥርዓቶችን ጥቀሱ::

**ግብይት ማለት:-**

- በተለያዩ ሰዎች በቡድን ወይም በግል የሚፈልጉትን ለማግኘት የሚያድርጉት ልውውጥ ወይም ግዥና ሽያጭ ሂደት ነዉ::
- ሸማቹን፣ ደንበኛውን እና ህዝቡን ከገበያ ጋር የሚያገናኝ ተግባር ነው::
- በግልጽ ደንበኛ ለመሳብ እና ለማግኘት ዋጋ ያለው፣ ተዛማጅ እና ወጥነት ያለው ይዘት የመፍጠር እና የማሰራጨት ዘዴ ነው::
- የገበያ ምርምርን እና ማስታወቂያዎችን ጨምሮ ምርቶችን ወይም አገልግሎቶችን የማስተዋወቅ እና የመሸጥ ተግባርን ያካትታል::

በአጠቃላይ የግብይት ሂደት በተቻለ መጠን የተጠቃሚዉን /የገዥዉን/ ፍላጎት ከአምራቹ የማምረት ችሎታና ዓላማ አጣጥሞ ሁሉንም ተዋናዮች በሚያረካ መልኩ የሚካሄድ ነዉ::



ሥዕል 4.6 ሰዎች ገበያ ሲገበያዩ

## 4.1.8. በዞናችሁ ለገበያ የሚቀርቡ የተፈጥሮ ሀብት እና ምርቶቻቸዉ

### የተግባር 4.10: የቡድን ዉይይት

**ዓላማ፡-** በዞናችሁ ለገበያ የሚቀርቡ የተፈጥሮ ሀብት እና ምርቶቻቸዉን መለየት

**መመሪያ፡-** በቡድን በመወያየት መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ

**የመወያያ ጥያቄዎች፡-**

1. በአካባቢያችሁ ለገበያ የሚቀርቡ የተፈጥሮ ሀብቶችን ዘርዝሩ።
2. የተፈጥሮ ሀብት ምርቶች ለሰዉ ልጅ ከሚሰጡት ጥቅሞች ጥቂቶቹን ጥቀሱ።

የተፈጥሮ ሀብቶች እና ምርቶቻቸዉ የሚባሉት በተፈጥሮ የምናገኛቸዉና ለሰዉ ልጅ ጥቅም የሚዉሉ ናቸዉ።

የተፈጥሮ ሀብት ለኅብረተሰቡ ከሚሰጧቸው ዋና ዋና ጥቅሞች ውስጥ

- ለምግብ ምንጭነት
- ለመጠለያ ግንባታ
- ለልብስ
- ለገቢ ምንጭነት፣ ወዘተ…

በተለያዩ አካባቢዎች የተለያዩ የተፈጥሮ ሀብቶች ይገኛሉ ከእነዚህም ዉስጥ ደን፣ ዉሃ፣ ቅመማቅመም፣ የነዳጅ ዘይት ወዘተ…ናቸዉ። ሰዎች እነዚህን የተፈጥሮ ሀብቶች በመጠቀም ግብይት ያከናዉናሉ።

## 4.1.9. በዞናችሁ የተፈጥሮ ሀብት እና ምርቶቻቸዉ የግብይት ልምዶች

### የተግባር 4.11: የቡድን ዉይይት

**ዓላማ፡-** በዞናችሁ የተፈጥሮ ሀብት እና ምርቶቻቸዉ የግብይት ልምዶችን መግለፅ

**መመሪያ፡-** በቡድን በመወያየት መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ

**የመወያያ ጥያቄ:-**

1. በአካባቢያችሁ ከተፈጥሮ ሀብት የሚገኙ ምርቶች ላይ የሚደረጉ የግብይት ልምዶችን ዘርዝሩ።

በምንኖርበት አካባቢ ከተፈጥሮ ሀብት የሚገኙ ምርቶች የግብይት ሥርዓት እና ልምድ ከቦታ ቦታ ሊለያይ ይችላል።በመሆኑም በተለያየ ማህበረሰብ ዉስጥ የተለያዩ የግብይት ልምዶችን በመከተል ግብይት ይከናወናል።በዚሁ መሰረት ገበያተኞች በገበያ ስልቶቻቸው ውስጥ የመደጋገፍ መርህ ይጠቀማሉ።

## 4.1.10. ለሰዎችና የሸቀጦች የመጓጓዣ መንገዶች

### የተግባር 4.12: የቡድን ዉይይት

**ዓላማ:-** የሰዎችና የሸቀጦች የመጓጓዣ መንገዶችን መለየት

**መመሪያ:-** በቡድን በመወያየት መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ

**የመወያያ ጥያቄዎች:-**

1. በምትኖሩበት አካባቢ ሰዎች ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ በምን ይጓዛሉ?
2. በምትኖሩበት አካባቢ ሰዎች ምርቶቻቸዉንም ሆነ ሸቀጣ ሸቀጦችን በምን ያጓጉዛሉ?

መጓጓዣ ማለት ሰዎችን፣ እንስሳትን እና ዕቃዎች ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለማንቀሳቀስ የሚረዳ መንገድ ነው። የመጓጓዣ ዓይነቶች የመሬት መጓጓዣ፣ የውሃ መጓጓዣ እና የአየር መጓጓዣ በመባል ይታወቃሉ።




ሥዕል 4.7 የተለያዩ መጓጓዣ አይነቶች

## መልመጃ 4.1

**ሀ. የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች ካነበባችሁ በኋላ ትክክል ከሆነ “እውነት” ትክክል ካልሆነ ደግሞ “ሀሰት” በማለት መልሱ።**

1. ባህል እና ቋንቋ የማይነጣጠሉ ናቸው።
2. መርከብ የዉሃ ላይ የመጓጓዣ ዓይነት ነዉ።

**ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛዉን መልስ የያዘ ሆሄ ምረጥ/ጭ/።**

1. ከሚከተሉት ዉስጥ አንዱ የተፈጥሮ ሀብት ነዉ?

   ሀ. ደን　　　　ሐ. መሬት

   ለ. ዉሃ　　　　መ. ሁሉም መልስ ናቸዉ

2. በእንስሳት እርባታ ዉስጥ የሚካተተዉ የቱ ነዉ?

   ሀ. በግ　　　　ሐ. ዓሳ

   ለ. ፍየል　　　　መ. ሁሉም መልስ ናቸዉ

**ሐ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛዉን መልስ ስጡ።**

1. በአካባቢያችሁ የተለመደዉን በባህላዊ አለባበስና በዘመናዊ አለባበስ መካከል ያለዉን ልዩነት ግለፁ።
2. ግጭት ማለት ምን ማለት ነዉ? በአካባቢያችሁ የተለመደ የግጭት አፈታት ስርዓትስ እንዴት ነዉ?

## ማጠቃለያ

- ባህል በማህበረሰብ መካከል የሚፈጠር የተለያዩ እሴቶችን ያካትታል፡፡
- የባህል ብዝሃነት የተለያዩ ባህሎች አንዳቸው የሌላውን ልዩነት ማክበርን ሊያመለክት ይችላል፡፡
- ባህላዊ አለባበስ የአንድን የተወሰነ ማህበረሰብ ማንነት ለመወከል ጥቅም ላይ የሚዉል የባህል መገለጫ ነዉ፡፡
- ባህላዊ የግጭት አፈታት ማለት በአንድ ማህበረሰብ ዉስጥ በግለሰብ ደረጃም ይሁን በቡድን የሚፈጠሩ ግጭቶችን(አለመግባባቶችን) ለመከላከል የሚረዳ በፅሁፍ ወይም በሰነድ ያልተቀመጠ ህግና ደንብ ነዉ፡፡
- ቋንቋ ሰዎች እርስ በርስ የሚግባቡበት፣ ግንኙነት የሚፈጥሩበት እና የማህበረሰብ ስሜት የሚፈጥሩበት መንገድ ነው፡፡
- የተፈጥሮ ሀብቶች ውስን እና ዘላቂነት በሌለው አጠቃቀም ሊጠፉ የሚችሉ ስለሆነ በአካባቢያችን የሚዘወተሩ ባህላዊ የተፈጥሮ አጠባበቅ ልምዶች ሊበረታቱ ይገባል፡፡
- ግብርና፣ እንዱስትሪ፣ ማዕድን ቁፋሮ፣ ንግድ፣ ትራንስፖርትና ቱሪዝም ዋና ዋናዎቹ ከሚባሉት የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ዉስጥ ጥቂቶቹ ናቸው፡፡
- የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች በተፈጥሮ ሀብት ላይ አዎንታዊና አሉታዊ ተፅዕኖ ይኖራቸዋል፡፡
- ግብይት ሸማቹን፣ ደንበኛውን እና ህዝቡን ከገበያ ጋር ያገናኛል፡፡
- የተፈጥሮ ሀብቶች ከሚሰጧቸዉ ምርቶች ዉስጥ ቅመማቅመም፣ ቡና፣ የነዳጅዘይት ወዘተ…ይካተታሉ፡፡
- በተለያየ ማህበረሰብ ዉስጥ የተለያዩ የግብይት ልምዶችን በመከተል ግብይት ይከናወናል፡፡
- ማጓጓዣ ሰዎችን፣ እንስሳትን እና ዕቃዎችን ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለማንቀሳቀስ ያገለግላል፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ መልመጃ/ የክለሳ ጥያቄዎች/

### ሀ. የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች አንብባችሁ ትክክል ከሆኑ "እዉነት" ትክክል ካልሆኑ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልስ/ሽ/፡፡

1. ባህል በተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች መካከል የሚፈጠር የተግባቦት ዘይቤ ነዉ፡፡
2. ግብርና የእንስሳት እርባታን ብቻ የሚያጠቃልል የምጣኔ ሀብት ዘርፍ ነው፡፡
3. የተፈጥሮ ሀብት ለሰዉ ልጅ ከሚሰጣቸዉ ጥቅሞች ምግብ አንዱ ነዉ፡፡
4. ሰዎች መርከብን ለመጓጓዣነት ይጠቀሙበታል፡፡
5. ኢንዱስትሪ የጎጆና ዘመናዊ ተብሎ ይከፈላል፡፡

### ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልስ/ሽ/፡፡

1. ከሚከተሉት ዉስጥ ባህላዊ ልምድ የሆነዉ የቱ ነዉ?
   - ሀ. ጋብቻ
   - ለ. አለባበስ
   - ሐ. የለቅሶ ስርዓት
   - መ.ሁሉም መልስ ናቸዉ
2. የመጓጓዣ ዓይነት የሆነዉ የቱ ነዉ?
   - ሀ. የአየር መጓጓዣ
   - ለ.የመሬት መጓጓዣ
   - ሐ.የዉሃ መጓጓዣ
   - መ. ሁሉም መልስ ናቸዉ
3. ከሚከተሉት ወስጥ አንዱ ዘመናዊ እንዱስትሪ ነዉ፡፡
   - ሀ.ፋብሪካ
   - ለ.ሽመና
   - ሐ.ሸክላ ስራ
   - መ.ሁሉም መልስ ናቸዉ
4. የአየር መጓጓዣ የሆነዉ የቱ ነዉ?
   - ሀ. መኪና
   - ለ. አዉሮፕላን
   - ሐ. መርከብ
   - መ. ባቡር

### ሐ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጫጭር መልሶችን ስጡ፡፡

1. ባህላዊ መገለጫዎች ምንድን ናቸዉ?
2. ባህላዊ ልምድ ከሚባሉት ዉስጥ ጥቂቶቹን ጥቀሱ፡፡
3. የሰዉ ልጅ የግጭት ምክንያቶችን ዘርዝሩ፡
4. የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ማለት ምን ማለት ነዉ፡?
5. የመጓጓዣ ዓይነቶችን ዘርዝሩ፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# የተለየ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህንን ርዕስ ካጠናቀቃችሁ በኋላ:-

- የትራፊክ ደንቦችን ትገልፃላችሁ።
- የትራፊክ ደንቦችን ትተገብራላችሁ።
- የኤች አይ ቪ/ እና ኤድስ ልዩነት ትገልፃላችሁ ።
- የኤች አይ ቪ/ኤድስ በሽታ ምልክቶችን ትለያላችሁ፡

## በምዕራፉ የተካተቱ ይዘቶች

5.1. የመንገድ ደህንነት

5.2. ኤች አይ ቪ/ኤድስ

## መግቢያ

በሁለተኛ ክፍል የአካባቢ ሳይንስ ትምህርታችሁ ስለመንገድ ደህንነት ምንነት እና የትራፊክ ደንቦችን እንዴት እንደምትተገብሩ እንዲሁም ኤች አይ ቪ/ ኤድስ ልጆች ላይ ያለዉን ተፅዕኖ እና ከኤች አይ ቪ/ኤድስ ጋር የሚኖሩ ልጆችን ችግር እንደራሳችን ችግር ማየት እንዳለብን ተምራችኋል።በዚህ ምዕራፍም የመንገድ ደህንነት እና ኤች አይ ቪ/ኤድስ የሚሉት ይዘቶች ተካተዋል። በመንገድ ደህንነት ሥር የትራፊክ ደንቦችን በመለየት እንዴት እንደምትተገብሯቸዉ በጥልቀት ትማራላችሁ። እንደዚሁም የመኪና አደጋ በልጆች እና በቤተሰብ ላይ የሚሳድረዉን ተፅዕኖ ትረዳላችሁ። በኤች አይ ቪ/

ኤድስ ርዕስ ሥር በኤች አይ ቪ እና ኤድስ መካከል ያለዉን ልዩነት እንዲሁም የኤች አይ ቪ/ኤድስ መተላለፊያ፣ መከላከያ መንገዶች እና የኤድስ በሽታ ምልክቶችን ትማራላችሁ፡፡በግል፣ በጥንድና በቡድን እየሆናችሁ በውይይት መማር ይጠበቅባችኋል፡፡

## 5.1. የመንገድ ደህንነት



### መታወስ የሚገባቸው ቁልፍ ቃላት፡-

- ☑ ግራ ጠርዝ
- ☑ ዜብራ
- ☑ የመኪና አደጋ
- ☑ የትራፊክ መብራት
- ☑ እግረኛ
- ☑ አሽከርካሪ

### ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች! ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፡-

- የትራፊክ ደንቦችን ትለያላችሁ፡፡
- የትራፊክ ደንቦችን ትተገብራላችሁ፡፡
- የመንገድ ማቋረጥ ደንቦችን በመለየት ሌሎችን መርዳት ትለማመዳላችሁ፡፡
- የመኪና አደጋ በልጆች እና በቤተሰብ ላይ የሚያሳድረዉን ተፅዕኖ ትገልፃላችሁ፡፡

### የመንገድ ደህንነት

#### የተግባር 5.1: የቡድን ዉይይት

ዓላማ፡- የትራፊክ ደንቦችን መለየት

መመሪያ፡- በቡድን በመወያየት መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ

የመወያያ ጥያቄዎች፡-

1. የመንገድ ደህንነት ማለት ምን ማለት ነዉ?
2. የምታወቋቸዉን የትራፊክ ደንቦችን ዘርዝሩ፡፡

የመንገድ ደህንነት ማለት በመንገድ ላይ በምንጓዝበት ጊዜ በተሽከርካሪ አደጋ እንዳይደርስብን የሚያስችሉን የጥንቃቄ እርምጃዎች ናቸዉ ።

የመንገድ ደህንነት የትራፊክ ደንቦችን በመከተል በእግረኛም ይሁን በአሽከርካሪ ላይ ሊደርሱ የሚችሉትን አደጋዎች ይከላከላል ወይም ይቀንሳል።

የትራፊክ ደንቦች የሚያካትታቸዉ:-

- የመኪና መንገድ ስናቋርጥ ጥንቃቄ ማድረግ
- እግረኞች የመኪና መንገዱን ግራ ጠርዝ ይዘዉ መጓዝ
- የትራፊክ መብራት ምልክቶችን ማወቅና መጠቀም
- አሽከርካሪዎችና እግረኞች የመንገድ ላይ የትራፊክ ምልክቶችን ማወቅና መጠቀም
- አሽከርካሪዎች ለእግረኞች ቅድሚያ መስጠት
- መኪና ውስጥ ሆነን በምንጓዝባቸው ጊዜያት ሁሉ የደህንነት/የጥንቃቄ/ ቀበቶ መታጠቅ፡ እና ወዘተ…

## የተግባር 5.2: የቡድን ዉይይት

ዓላማ:- የመኪና መንገድ ስናቋርጥ ማድረግ ያለብንን ጥንቃቄ መለየት

መመሪያ:- በቡድን በመወያየት መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ

የመወያያ ጥያቄ:-

1. እግረኞች የመኪና መንገድ ሲያቋርጡ ማድረግ ያለባቸዉን ጥንቃቄዎች ዘርዝሩ።

እግረኞች መኪና በሚንቀሳቀስባቸው መንገዶች ሲያቋርጡ የጥንቃቄ እርምጃዎች መፈፀም ይኖርባቸል።

እነዚህም:-


- የመኪና መንገድ በምናቋርጥበት ጊዜ የእግረኛ ማቋረጫ ነጭናጥቁር ቀለም /ዜብራ/ የተቀባበት ምልክት ላይ በመጓዝ ማቋረጥ።
- የእግረኛ ማቋረጫ ነጭናጥቁር ቀለም /ዜብራ/ ምልክት ከሌለ በአጭሩና በቀጥተኛው አቅጣጫ የተሽከርካሪዎችን ሁኔታ በጥንቃቄ በማየት በፍጥነት ማቋረጥ ይገባናል

- መንገድ ሲናቋርጥ መጀመሪያ ወደ ግራና ቀኝ በማየት በቅርብ ርቀት መኪና አለመኖሩን አረጋግጠን ይበልጥ ጥንቃቄ በማድረግ ማቋረጥ፡፡
- የመኪና መንገድ ሲናቋርጥ በመንገድ መካከል አለመቆም፣አለመቀመጥ ወይም አለመጫወት
- በመስቀለኛ መንገድ ወይም በአደባባይ ላይ በሰያፍ ያለማቋረጥ

## የማነቃቂያ ጥያቄ

ከዚህ በታች የቀረቡትን ሥዕሎች በጥንቃቄ ተመልከቱና ቀጥሎ ለተመለከቱት ጥያቄዎች ለመምህራችሁ መልስ መልሱ፡፡

1. ልጆቹ ምን እያደረጉ ነዉ?
2. የትኛዉ ሥዕል ትክክለኛዉን የትራፊክ ደንብ ያሳያል? ለምን?
3. የትኛዉ ሥዕል ትክክለኛዉን የትራፊክ ደንብ አያሳይም? ለምን?



ሥዕል 5.1 ሀ



ሥዕል 5.1 ለ

## የመንገድ ላይ የትራፊክ መብራት ጠቀሜታ

### የተግባር 5.3: የቡድን ዉይይት

**ዓላማ:-** የትራፊክ መብራት ምልክቶችን ማወቅና መጠቀም

**መመሪያ:-** በቡድን በመወያየት መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ

**የመወያያ ጥያቄዎች:-**

1. የመንገድ ላይ የትራፊክ መብራት ጥቅም አብራሩ::
2. የመንገድ ላይ የትራፊክ ስነስርዓት ማስጠበቂያ የመብራት ቀለም ዓይነቶችን ዘርዝሩ::

የመንገድ ላይ የትራፊክ ስነስርዓት ማስጠበቂያ የመብራት ምልክቶች የሚሠሩት በኤሌክትሪክ ኃይል ሲሆን፣ የመኪና እና የእግረኛ እንቅስቃሴ አደጋ በማይፈጥርበት ሁኔታ እንዲከናወን እገዛ ያደርጋሉ::

የመንገድ ላይ የትራፊክ ማስተላለፊያ መብራቶች ሶስት ዓይነት ቀለም ያላቸው ሲሆኑ እነሱም:- አረንጓዴ፣ ቢጫ እና ቀይ ናቸው::

- አረንጓዴ መብራት ሲበራ መኪናዎች እንዲተላለፉ መፍቀጃ በመሆኑ አረንጓዴ የመንገድ መብራት ሲበራ እግረኞች የመኪና መንገዱን ለማቋረጥ መሞከር የለባቸውም::
- ቢጫው መብራት የሚያመለክተው ቀጣዩ የመብራት ምልክት ቶሎ ሊበራ እንደሚችል ማስጠንቀቂያ በመሆኑ እግረኞችም ሆኑ አሽከርካሪዎች ጥንቃቄ እንዲወስዱ ማሳሰቢያ ነው::
- ቀይ መብራት በሚበራበት ጊዜ መኪናዎች መንቀሳቀስ ያቆማሉ:: ለአሽከርካሪዎች የቀዩ መብራት የሚያመለክተው እንዲያቆሙ በመሆኑ፣ እግረኞች ተገቢውን ጥንቃቄ አድርገው መንገዱን ሊያቋርጡ ይችላሉ፡

## የተግባር ጨዋታ ለተማሪዎች

**ዓላማ:-** የትራፊክ ደንቦችን በመከተል ተማሪዎች ጥንቃቄ እንዲያደርጉ

መመሪያ:-በሁለት ምድብ በመከፈል የመጀመሪያው ምድብ ውስጥ ያላችሁ ልጆች የኮከብ ምልክት (*) የተደረገበትን ሀረግ ሲዘምሩ፣ በሁለተኛው ምድብ ያላችሁ ልጆች በመደመር (+) ምልክት ስር የተፃፈውን የግጥም ሀረግ በመዘመር እየተቀባበላችሁ መዝሙሩን ዘምሩ:: መዝሙሩን ክፍል ውስጥ ብቻ ሳይሆን ለወላጆቻችሁ እና

ለታላላቆቻችሁ ጭምር ዘምራችሁ በማሰማት ጠንቃቃ ልጆች መሆናችሁን ግለፁላቸው::

መዝሙር

## ከአደጋ እንጠበቅ

* ተሽከርካሪ የሚጓዘው
\+ በጐማ ነው፣ በጐማ ነው::
* የሰው ልጅ ሚጠቀመው፣
\+ በእግሩ ነው፣ በእግሩ ነው::
* ፍጥነት አለው ተሽከርካሪ፣
\+ ካለው በላይ ነው በራሪ::
* መጠንቀቅ ነው የሚያድነን፣
\+ በመንገድ ላይ ከአደጋ እንድንድን::
* አዎን ልጆች እንጠንቀቅ፣ እንጠንቀቅ
\+ ራሳችንን ከአደጋ እንጠብቅ፣ እንጠብቅ::
* ራሳችንን ከአደጋ፣ እንጠብቅ፣ እንጠብቅ::

ምንጭ:- ከ1ኛ ክፍል እስከ 4ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች የመንገድ ደህንነት ግንዛቤን ለማዳበር የተዘጋጀ መማሪያ ካሪኩለም ጋይድ

የመኪና አደጋ በቤተሰብና በልጆች ላይ የሚያደርሰዉ ተፅዕኖ

### የተግባር 5.4: የቡድን ዉይይት

ዓላማ:- የመኪና አደጋ በቤተሰብና በልጆች ላይ የሚያደርሰዉ ተፅዕኖ መለየትና ማወቅ

መመሪያ:- በቡድን በመወያየት መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ

የመወያያ ጥያቄ:-

1. የመኪና አደጋ በልጆች እንዲሁም በቤተሰብ ላይ የሚያስከትለዉን ተፅዕኖ በዝርዝር ተናገሩ::

በጥንቃቄ ጉድለት ምክንያት የሚከሰተዉ የመኪና አደጋ በልጆች፣ በቤተሰብ እና በሕብረተሰቡ ላይ ብዙ ተፅኖዎችን ያሳድራል::የመኪና አደጋ በልጆች እንዲሁም በቤተሰብ ላይ ከሚያደርሰዉ ተፅዕኖዎች መካከል:-

- የአዕምሮ ጭንቀትና የስሜት መረበሽ
- ፍርሀትና ድንጋጤ
- ስብራት
- የአካል መጉደል ወይም የተጎዳዉ የአካል ክፍል በትክክል አለመስራት
- ሞት
- በአደጋዉ የሞቱት ወላጆች ከሆኑ ልጆች ወላጆቻቸዉን ያጣሉ
- ወላጅ በማጣት ከትምህርት ማቋረጥ
- በአደጋዉ የተጎዳዉን የቤተሰብ አባል ለማሳከም ለህክምና ወጭ መዳረግ
- የተጎዳዉን ቤተሰብ ለማሳከም ከሥራ መቅረት
- በመኪና አደጋዉ ሞት ምክንያት የቤተሰብ አባል መጉደል....ወዘተ የመሳሰሉት የመኪና አደጋ በደረሰባቸዉ ልጆች ወይም ቤተሰብ ላይ የሚደርሱ ተፅኖዎች ናቸዉ።

በአጠቃላይ በጥንቃቄ ጉድለት ምክንያት የሚከሰት የመኪና አደጋ በልጆች፣ በቤተሰብ እና በሕብረተሰቡ ላይ የጤና፣አካላዊና የንብረት ጉዳት ያደርሳል።

## 5.2. ኤች አይ ቪ/ ኤድስ



### መታወስ የሚገባቸው ቁልፍ ቃላት:-

- ☑ ነጭ የደም ህዋስ
- ☑ የሰዉነት ፈሳሾች
- ☑ የደም ንክኪ
- ☑ መታቀብ
- ☑ ኤድስ
- ☑ ቫይረስ

### ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ:-

- የኤች አይ ቪ እና የኤድስ ልዩነት ትገልፃላችሁ ።
- የኤች አይ ቪ በሽታ ምልክቶችን ትዘረዝራላችሁ።
- የኤች አይ ቪ በሽታ መድሃኒቶችን ትለያላችሁ።

### የተግባር 5.5: የቡድን ዉይይት

**ዓላማ:-** የኤች አይ ቪ እና ኤድስን ምንነት መግለፅ

**መመሪያ:-** በቡድን በመወያየት መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ

**የመወያያ ጥያቄዎች:-**

1. የኤች አይ ቪ እና የኤድስን ልዩነት ዘርዝሩ፡፡
2. የኤች አይ ቪ ቫይረስ የሚገኝባቸዉን የሰዉነታችን ክፍሎች ግለፁ፡፡

ኤች አይቪ ቫይረስ ነው፡፡ ይህ ቫይረስ በዓይን የማይታይ ረቂቅ ሕዋስ ሲሆን የሚያጠቃውም በሽታ ተከላካይ የሆነውን የሰዎች ነጭ የደም ሕዋስ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት ሰውነታችን ተፈጥሯዊ የበሽታ መከላከያ ሃይልን ሲያጣ በቀላሉ በበሽታ ይጠቃል፡፡በመሆኑም የሰውነታችን በሽታን የመከላከል አቅም ሲዳከም በቀላሉ ወደ ኤድስ በሽተኛነት ይቀየራል፡፡

**ይህ ቫይረስ በበሽታው በተያዙ ሰዎች :-**

- ደም ውስጥ
- በወንድና በሴት የመራቢ አካላት ፈሳሽ ውስጥ
- በጡት ወተት ውስጥ እና
- በቫይረሱ ተበከሉ ሹልና ስለታም ነገሮች /መርፌ ፣ምላጭ / ውስጥ ይገኛል፡፡

ኤድስ ኤች አይ ቪ በሚባል በሽታ አምጪ ቫይረስ የሚከሰት የሰውነትን በሽታ የመከላከል አቅም ቀስ በቀስ በማዳከም ለሞት የሚዳርግ በሽታ ነው፡፡

## የተግባር 5.6: የቡድን ዉይይት

**ዓላማ:-** የኤች አይ ቪ/ኤድስ በሽታ መተላለፊያ እና መከላከያ መንገዶችን መለየት

**መመሪያ:-** በቡድን በመወያየት መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ

**የመወያያ ጥያቄዎች:-**

1. የኤች አይ ቪ ቫይረስ ከበሽተኛው ወደ ጤናማ ሰዉ የሚተላለፍባቸዉን መንገዶች ዘርዝሩ፡፡
2. ኤች አይ ቪ ከበሽተኛው ወደ ጤናማ ሰዉ እንዳይተላለፍ መከላከያ መንገዶችን ጥቀሱ፡፡
3. የኤች አይ ቪ/ኤድስ በሽታ ዋና ዋና ምልክቶች ምንድን ናቸዉ?

ኤች አይ ቪ/ኤድስ ከበሽተኛው ወደ ጤናማ በሚከተሉት መንገዶች ሊተላለፍ ይችላል፡፡

- ጥንቃቄ የጎደለው የግብረ ሥጋ ግንኙነት ወይም ወሲብ
- በደም ልገሳ/ቫይረሱ በደሙ ያለበት ሰዉ ለጤናማ ሰዉ ደም ከለገሰ
- ከእናት ወደ ልጅ /በወሊድ ጊዜ ወይም በማጥባት/
- በኤች አይቪ ቫይረስ የተበከሉ ስለታም ነገሮችን በጋራ በመጠቀም ሊተላለፍ ይችላል፡፡

የኤች አይ ቪ/ኤድስ በሽታ ዘር ፣ፆታ ፣ሐይማኖትና ዕድሜ ሳይለይ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል ሊያጠቃ የሚችል በሽታ ነዉ፡፡በመሆኑም ዋና ዋና የኤች አይ ቪ/ኤድስ የመከላከያ መንገዶችን ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ እነዚህም የሚከተሉት ናቸዉ:-

- መታቀብ:- ከጋብቻ በፊት ከግብረ ሥጋ ግንኙነት መቆጠብ
- አንድ ለአንድ መወሰን /አንድ ወንድ ለአንዲት ሴት በትዳር ፀንቶ መኖር/
- አንዱ የተጠቀመበትን ሹልና ስለታም መሣሪያዎች ሌላ ሰው እንዲይጠቀም ማድረግ
- በጋራ የጥርስ ብሩሽ አለመጠቀም

- በደንብ ባልተቀቀለ የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች አለመጠቀም
- ከቫይረሱ ጋር የምትኖር እናት ቫይረሱ በእርግዝና ወቅት ወደ ጽንሱ እንዳይተላለፍ መጠንቀቅና የቅርብ ሕክምና ክትትል ማድረግ

ከላይ የተጠቀሱትን ተግባራት በትክክል ከተከናወኑ በበሽታዉ የተጠቁ ሰዎች በቅድሚያ እራሣቸውን በመከላከል ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡ በመቀጠልም ቫይረሱ ወደ ሕብረተሰቡ እንዳይሠራጭ ስለሚረዱ አገራዊ ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው፡፡

በኤች አይ ቪ ቫይረስ ምክንያት የሰዉነታችን በሽታ መከላከል አቅም ሲዳከም በቫይረሱ በተያዙ ሰዎች ላይ ዋናው የኤች አይ ቪ ምልክቶች ይታያሉ፡፡ እነዚህም የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

- በተደጋጋሚ ከፍተኛ ትኩሳት
- ድካም ወይም ኃይልን ማጣት
- ራስ ምታት
- የጉሮሮ ህመም(ጉሮሮ አካባቢ ያሉ ዕጢዎች ህመም)
- የሌሊት ላብ
- ከፍተኛ የሆነ የክብደት መቀነስ
- ተቅማጥ(ለረጅም ጊዜ ከሆነ)
- የቆዳ ላይ ሽፍታ

ለኤች አይ ቪ የተጋለጡ ሰዎች እንዲህ ዓይነቱ ግልጽ የሆነ የኤች አይ ቪ / ኤድስ ምልክት ኤች አይ ቪን ለመመርመር የሚያመላክት ምክንያት ነው፡፡

ኤድስ ከቫይረሱ ባህሪይ መቀያየር አንፃር እስካሁን መድሃኒት ያልተገኘለት በሽታ ነዉ፡፡ነገር ግን ፀረ-ኤች አይ ቪ መድሃኒቶች ኤች አይ ቪ ቫይረስ በሰዉነታችን ዉስጥ እንዳይራባ ዕድገቱን በመግታት በሽታዉ የሚያመጣዉን ጉዳት ይቀንሳሉ፡፡በመሆኑም የፀረ-ኤች አይ ቪ መድሃኒቶች የቫይረሱን መራባት በማቆም ወይም በመግታት፣ የቫይረሱን መጠን በደም ዉስጥ እንዲቀንስ በማድረግ፣ወደ ሌላ ሰዉ የቫይረሱን መተላለፍ ዕድል በመቀነስ እና ለሌሎች ተጓዳኝ በሽታዎች ለመጋለጥ የሚኖረዉን ዕድል በመቀነስ በቫይረሱ የተያዙትን ሰዎች ጤንነት የተሻለ እንዲሆን ይረዳሉ፡፡

## ማጠቃለያ

- የመንገድ ደህንነት የትራፊክ ደንቦችን በመከተል በእግረኛም ይሁን በአሽከርካሪ ላይ ሊደርሱ የሚችሉትን አደጋዎች ይቀንሳል፡፡
- አሽከርካሪዎችና እግረኞች የመንገድ ላይ የትራፊክ ምልክቶችን ማወቅና መጠቀም ይጠበቅባቸዋል፡፡
- የመኪና መንገድ በምናቋርጥበት ጊዜ የእግረኛ ማቋረጫ ነጭ እና ጥቁር ቀለም /ዜብራ/ የተቀባበት ምልክት ላይ በመጓዝ ማቋረጥ አለብን፡፡
- መኪና ውስጥ ሆነን በምንጓዝባቸው ጊዜያት ሁሉ የደህንነት/ የጥንቃቄ/ ቀበቶ መታጠቅ አለብን፡፡
- የመንገድ ላይ የትራፊክ ስነስርዓት ማስጠበቂያ የመብራት ምልክቶች የመኪና እና የእግረኛ እንቅስቃሴ አደጋ በማይፈጥርበት ሁኔታ እንዲከናወን እገዛ ያደርጋሉ፡፡
- በአጠቃላይ በጥንቃቄ ጉድለት ምክንያት የሚከሰት የመኪና አደጋ በልጆች፣ በቤተሰብ እና በሕብረተሰቡ ላይ የጤና፣አካላዊና የንብረት ጉዳት ያደርሳል፡፡
- ኤች አይ ቪ ቫይረስ ነው፡፡ ይህ ቫይረስ በዓይን የማይታይ ረቂቅ ሕዋስ ሲሆን የሚያጠቃውም በሽታ ተከላካይ የሆነውን የሰዎች ነጭ የደም ሕዋስ ነው።
- ኤድስ ኤች አይ ቪ በሚባል ቫይረስ የሚከሰት የሰውነትን በሽታ የመከላከል አቅምን ቀስ በቀስ በማዳከም ለሞት የሚዳርግ በሽታ ነው፡፡
- በኤች አይ ቪ ቫይረስ ምክንያት የሰዉነታችን በሽታ መከላከል አቅም ሲዳከም በቫይረሱ በተያዙ ሰዎች ላይ ዋናው የኤች አይ ቪ ምልክቶች ይታያሉ፡፡
- ፀረ-ኤች አይ ቪ መድሃኒቶች ቫይረሱን በሰዉነታችን ዉስጥ እንዳይራባ ዕድገቱን በመግታት በሽታዉ የሚያመጣዉን ጉዳት ይቀንሳሉ፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ መልመጃ/ የክለሳ ጥያቄዎች/

### ሀ. ትክክለኛ የሆነውን ሀሳብ "እውነት" ትክክለኛ ያልሆነውን "ሐሰት" በማለት መልስ/ሽ/፡፡

1. የመኪና አደጋ የሚደርሰው ተገቢውን የመንገድ አጠቃቀም ስርዓት ስንከተል ነው፡፡
2. በመንገድ ላይ የተተከሉ የትራፊክ የመብራት ምልክቶች የሚያገለግሉት ለተሽከርካሪዎች እንቅስቃሴ ብቻ ነው፡፡
3. በሞተር ኃይል የሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎች ከፍተኛ አደጋ ሊያደርሱብን ይችላሉ፡፡
4. በመንገድ ላይ የተተከሉ የመብራት ምልክቶች የሚሰሩት በኤሌክትሪክ ኃይል እገዛ ነው፡፡
5. ቢጫ የትራፊክ መብራት ሲበራ እግረኞችም ሆኑ ተሽከርካሪዎች መንገዱን ሊያቋርጡ ይችላሉ፡
6. ኤች አይ ቪ ቫይረስ የሚያጠቃው በሽታ ተከላካይ የሆነውን የሰዎች ነጭ የደም ህዋስ ነው።
7. በኤች አይ ቪ ቫይረስ ምክንያት የሰዉነታችን በሽታ መከላከል አቅም ይዳከማል፡፡

### ለ.. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልሱ፡፡

1. ተሽከርካሪዎች የሚንቀሳቀሱት በምን ሀይል ነው፡፡
   - ሀ. በሞተር ሀይል
   - ለ. በሰው ኃይል
   - ሐ. በእንስሳት ኃይል
   - መ. ሁሉም
2. አደጋ እንዳይደርስባቸው እግረኞች መዉሰድ ያለባቸው ጥንቃቄ
   - ሀ. የመኪና መንገድ ውስጥ ገብቶ መጓዝ
   - ለ. የመንገዱን ቀኝ ጠርዝ ይዞ መሄድ
   - ሐ. የእግረኛ መንገድ ይዞ መጓዝ
   - መ. ተገቢውን ጥንቃቄ አለማድረግ
3. የመኪና አደጋ ሊደርስ የሚችለው
   - ሀ. አሽከርካሪዎች ጥንቃቄ ስለሚያደርጉ
   - ለ. ሳይጠነቀቁ እግረኞች በመኪና መንገድ ውስጥ ገብተው የሚጓዙ ከሆነ

ሐ. መኪና አለመኖሩን ሳያረጋግጡ የመኪና መንገድን ለማቋረጥ በሚደረግ ሙከራ

መ. ለ እና ሐ መልስ ይሆናሉ

4. የመኪና አደጋ ምን ያስከትላል?

ሀ. ህይወት ያሳጣል

ለ. አካለ ጉደሎ እንድንሆን ሊያደርገን ይችላል

ሐ. የቤተሰባችን ቁጥር ያጎላል

መ. ሁሉም መልስ ይሆናሉ

5. ኤች አይ ቪ በሰዉነታችን በየትኛዉ ፈሳሽ ዉስጥ ይገኛል?

ሀ. በደም

ለ. በጡት ወተት

ሐ. የመራቢ አካላት ፈሳሽ

መ. ሁሉም መልስ ይሆናሉ

6. የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያ መንገድ ያልሆነዉ የቱ ነዉ?

ሀ. መታቀብ

ለ. በአንድ ጓደኛ መወሰን

ሐ. በጋራ የጥርስ ብሩሽ መጠቀም

መ. ስለታም ነገሮችን በጋራ አለመጠቀም